# የስነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅድ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአፈጻጸም መመሪያ

*በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የፋ/ኢ/ል/ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ማስተባበርና መተግበር ዋና የስራ ሂደት የተዘጋጀ*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም*
*ሀዋሣ*

# ማውጫ

ክፍል አንድ


1.1 መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------1

1.2 ዓላማ-------------------------------------------------------------------------------2

1.3 አስፈላጊነት---------------------------------------------------------------------------3

1.4 የክልሉ የስነ-ሕዝብና ልማት ገፅታ--------------------------------------------------3

1.5 የስነ-ሕዝብና ልማት ትስስር ምንነት-----------------------------------------------6

1.6 ስትራቴጂክ ጉዳዮች-------------------------------------------------------------------8

ክፍል ሁለት የስነ-ሕዝብና ልማት ትስስር------------------------------------------------10

2.1 ስነ-ሕዝብና ትምህርት -------------------------------------------------------------------10

2.1.1 ስነ-ሕዝብ በትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ-----------------------------------11

2.1.2 ትምህርት በስነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ-----------------------------------16

2.1.3 በትምህርት ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች--------------------------------------------17

2.2 ስነ-ሕዝብና ጤና--------------------------------------------------------------------------20

2.2.1 ስነ-ሕዝብ በጤና ላይ ያለው ተፅዕኖ-----------------------------------------23

2.2.2 ጤና በስነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ

2.2.3 ጤና ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች--------------------------------------------25

2.3 ስነ-ሕዝብ፣ግብርናና የአካባቢ ጥበቃ-----------------------------------------------27

2.3.1 ስነ-ሕዝብ በግብርና ላይ ያለው ተፅዕኖ--------------------------------------27

2.3.2 ግብርና በስነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ---------------------------------------30

2.3.3 በግብርና ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች---------------------------------------------25

2.4 ስነ-ሕዝብና ሥርዐተ-ፆታ-------------------------------------------------------32
2.4.1 ስነ-ሕዝብ በሥርዐተ-ፆታ ላይ ያለው ተፅዕኖ----------------------------32
2.4.2 ሥርዐተ-ፆታ በስነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ----------------------------33
2.4.3 በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ በሚቀረፁ ኘሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ---------34

2.5 ስነ-ሕዝብና ወጣቶች-----------------------------------------------------------35
2.5.1 ስነ-ሕዝብ በወጣቶች ላይ ያለው ተፅዕኖ---------------------------------35
2.5.2 በወጣቶችና ስፖርት ጉዳዩ ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ
ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች---------39

2.6 ስነ-ሕዝብና ማኀበራዊ ችግሮች-------------------------------------------------40
2.6.1 ስነ-ሕዝብ በማህበራዊ ችግሮች ላይ ያለው ተፅዕኖ---------------------40
2.6.2 ማህበራዊ ችግሮች በስነ-ሕዝብ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ--------------------41
2.6.3 በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሚቀርፀው ኘሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ
ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች------------43

ክፍል ሦስት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት-------------------------------------------45
3.1 ክትትል--------------------------------------------------------------------46
3.2 ግምገማ--------------------------------------------------------------------47
3.3 የሪፖርት አቀራረብና ግብረ-መልስ-----------------------------------------49

## 1. መ ግ ቢ ያ

ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያልተመጣጠነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማድረግ ለእድገት የሚደረጉ ሩጫዎችን ይገታል፡፡ ይህም የሚሆነው ለኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ ሀብቶችን በሚሚጠጥ ድህነት ሥር እንዲሠድ በማድረግ ለሕዝብ ኑሮ መሻሻል የሚደረገውን ጥረት የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ ተፅዕኖ በማድረግ ነው፡፡ የነፍስ ወከፍ ገቢን ከፍ የሚያደርገውን አጠቃላይ ምርታማነት በእጅጉ ለማሣደግ ቢሞክር እንኳን ተካፍሎ ውጤት የሚመጣበት የሕዝብ ቁጥር ካልተመጣጠነ በቀር የታለመውን ዕድገት ማምጣት አይቻልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ያልተመጠነ የሕዝብ ዕድገት ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን በበቂ ሁኔታ ለማዳረስ እንቅፋት ይሆናል፡፡

በየአመቱ በ2ሚሊዮን ያህል የሚያድገው የሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር በሀገሪቱ ማኀበራዊ አገልግሎቶችን እና የመሠረተ ልማትን ለማስፋፋት እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት እያስተጓጐለ ይገኛል፡፡ የደቡብ ክልልን ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ከሀገሪቱ ብዙም የራቀ አይደለም የክልሉ ሕዝብ በአመት በ29 በመቶ በማደግ በ1994 ዓ.ም. በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ 10,377,028 የነበረው የህዝብ ቁጥር በ13 አመት ውስጥ 4,665,503, በመጨመር በ2007 ዓ.ም. 15,042,,531 ደርሷል፡፡ ይህም የክልሉ ሕዝብ ላለፉት 13 አመታት በየአመቱ በአማካይ በ358,,885 ሰው እየጨመረ እንደሚሄድ ያመለክታል፡፡

ይህ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣው የህዝብ ቁጥር በክልሉ በሚካሄዱ የመሠረተ ልማት፣ ጤና፣ ትምህርትና ሌሎችም ማኀበራዊ አገልግሎቶች ላይ የራሱን ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡ ይህንን ጫና ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ ከልማት እንቅስቃሴ ጐን ለጐን የህዝቡን ቁጥር እድገት መግታት የሚያስችል የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ የሀገሪቱ መንግሥት ቀርጾ በክልላችንም እየተተገበረ ይገኛል፡፡

ሥነ-ሕዝብ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርናና ከሌሎችም ሴክተሮች ጋር ጠንካራ ቁርኝት አለው፡፡ ይህ ቁርኝትም አንዱ በአንዱ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖዎች እንዲኖሩት ያደርጋል፡፡ የሕዝብ ሥርጭት፣ቁጥር፣ የዕድሜና የፆታ ስብጥር እንዲሁም ተዛማጅ ጉዳዮች ያልዳሰሰ የትምህርትም ሆነ የጤና ልማት እንቅስቃሴ ግቡን ሊመታ አይችልም፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የልማት እቅድ ሲታቀድ የሥነ-ሕዝብ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት የግድ ይላል፡፡

በመሆኑም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በአንድ መሥሪያ ቤት ብቻ ተሠርቶ የሚጠናቀቅ ተግባር ሳይሆን ሁለገብ በሆነ መልኩ ለልማት መፋጠን አስፈላጊ ሚና በሚጫወቱ የልማት ክፍሎች አማካኝነት የሚተገበር በመሆኑ በሥነ-ሕዝብና ዘላቂ ልማት መካከል ያለውን ጥልቅ መስተጋብር በመረዳትና በቅንጅት በመሥራት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይገባል፡፡

ይህም የሚሆነው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በእያንዳንዱ ሴክተር የልማት ዕቅድ ውስጥ በማካተትና አፈጻጸሙንም በትኩረት በመከታተልና በመገምገም ነው፡፡ ለዚህ አላማ ሲባል ይህ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅድ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ መመሪያ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነት፣ የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ገጽታና ስትራቴጂክ ጉዳዮችን አጠቃሏል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ሥነ-ሕዝብ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርናና አካባቢ ጥበቃና፣ ከሥርዓተ ፆታ፣ ከወጣቶች እና ከማኀበራዊ ችግሮች ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም እነዚህ ሴክተሮች በኘሮግራሞቻቸውና እቅዶቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ ማድረግ ስለሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ያብራራል፡፡ ሦስተኛው ክፍል የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን የያዘ ክፍል ነው፡፡

## <u>1. 2. ዓላማ</u>

### <u>2.1 ጥቅል ዓላማ</u>

የዚህ የአፈጻጸም መመሪያ አጠቃላይ ዓላማ በክልሉ የሚገኙ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የሚተገበርባቸው ሴክተር መ/ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በእቅዶቻቸው ውስጥ አካተው ውጤታማ በሆነ መልኩ በመተግበ የክልሉን የልማት እድገት ከህዝብ ቁጥር እድገት ጋር ተጣጥሞ እንዲካሄድ ማስቻል ነው፡፡

### <u>2.2 ዝርዝር ዓላማ</u>

- የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ከተለያዩ ሴክተሮች ጋር ያላቸውን ትስስር ሴክተሮች በተገቢው ሁኔታ እንዲረዱት ማድረግ፣
- በዚህ የማስፈጸሚያ ማኑዋል አማካይነት ሴክተር መ/ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ማስቻል፣

- ጠንካራና ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የስነ-ሕዝብ ጉዳይ በሁሉም የልማት አጋሮች እንዲተገበር ማስቻል፣

## 1.3 የማኑዋሉ (የመመሪያው) ዝግጅት አስፈላጊነት

የሥነ-ሕዝብ ችግር መፍታት የሚቻለው በአንድ ወይንም በሁለት ሴክተር መ/ቤቶች የተናጥል እንቅስቃሰ ብቻ ሳይሆን የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በሚመለከታቸው ሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች የተቀናጀ ንቁ ተሣትፎ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው በሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው ላይ በተቀመጠው ስትራቴጂ መሠረት በሁሉም ሴ/ር መ/ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን አካቶ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡

ለዚህም ሴክተር መ/ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር ያለውን ትስስር ተገንዝበውና በእቅዶቻቸው ውስጥ አካተው መተግበር የሚያስችላቸው የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የአፈጻጸም ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.4 የክልሉ የሥነ-ሕዝብና ልማት ገጽታ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከኦሮሚያ ክልል በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ፣ ከጋምቤላ በሰሜን ፣ከሱዳን በደቡብ ምዕራብ እና ከኬንያ በደቡብ ይዋሰናል፡፡ ክልሉ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ቆዳ ስፋት 10% (110,932 ስኩዌር ኪ.ሜ) ብቻ የያዘ ቢሆንም ባሁኑ ወቅት የህዝቡ ቁጥር ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ሕዝብ 20.4% (15.04 ሚሊዮን) የያዘ መሆኑ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት እንዳለው ይመሰክራል፡፡ የደ/ብ/ብ/ብ/ሕ/ክልል አጠቃላይ የህዝብ ጥግግት መጠን ሲታይ በአማካይ በእያንዳንዱ ካሬ ኪ.ሜ 136 ሰው የሰፈረበት ሲሆን ይህም ከብሔራዊ አማካይ (67 ሰው/ካሬ ኪ.ሜ) ከእጥፍ በላይ የበለጠ ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የኢትዮጵያ አማካይ የእርሻ ጥግግት መጠን 5.4 ሰው በእያንዳንዱ ሄክታር የሰፈረ ሲሆን በክልሉ ግን በእያንዳንዱ ሄክታር 9.8 ሰው ተጨናንቆ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ክልሉ በሕዝብ ቁጥር ብዛት ጋር በተያያዘ ከሌሎች ከሀገሪቱ አካባቢዎች ይልቅ በከፍተኛ የሥነ-ሕዝብና ልማት ችግሮች ውስጥ እንዳለ ያመለክታል፡፡ ይህም ሁኔታ ኀብረተሰቡ በምግብ እህል ራሱን እንዳይችል ያደርጋል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የክልሉ የአንዲት ሴት በውልደት ዘመኗ የምትወልዳቸውን አማካይ የልጆች ቁጥር (TFR) ብንመለከት ደግሞ ባሁኑ ጊዜ 5.6 ልጆች እንደሆኑ ጥናቶች የጠቆሙ ሲሆን ይህም በሀገሪቱ ደረጃ ከፍተኛ ከሚባሉት አንዱ ከመሆኑ በተጨማሪ ከብሔራዊው አማካይ

(5.4 ልጅ) የበለጠ ነው፡፡ ነገሩን አሳሳቢ የሚያደርገው የገጠር ሴት ውልደት መጠን 6 ልጅ መሆኑ ሲሆን የክልሉ 90% የሚሆን ህዝብ የገጠሩ ነዋሪ ከመሆኑ አንፃርና በነዚህ ሥፍራዎች የተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ባብዛኛው ያልተዳረሱ በመሆናቸው እንዳሁኑ ሁሉ የክልሉ ሕዝብ ለወደፊቱ ባሉ አያሌ አመታትም ቢሆን ፈጣን ዕድገት እንደሚያሣይ አመላካች ነው፡፡

በክልሉ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ገና 11.9% ሲሆን አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈልጉት ሴቶች መጠን 37.4% መሆኑ ኀብረተሰቡ የሚፈልገውን ያህል የተዋልዶ ጤናና የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ለማሳካት ገና ረጅም መንገድ እንደሚቀር ያሳያል፡፡
አሁን ያለውን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፍላጎት (demand) ማሟላት ቢቻል ኖሮ የክልሉ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋን (CPR) 49% ይደርስ እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

ይህ ባለመሆኑ ምክንያት ብዙ እናቶችና ህፃናት ያለዕድሜ የመሞትና በህመም የመሰቃየት ችግር ውስጥ እንደወደቁ ምሁራን በመረጃ የተደገፈ ጥቆማዎችን ያቀርባሉ ባሁኑ ጊዜ በክልሉ 100,000 ከሆኑ ወላድ እናቶች ውስጥ ከእርግዝናና ከውልደት ሂደት ጋር በተያያዙ ችግሮች የተነሣ 671 የሚሆኑት ያለዕድሜአቸው ይሞታሉ፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ ከሚወለዱት ከ1000 ሕፃናት መካከል 85ቱ የመጀመሪያ አመት በዓላቸውን ሳያከብሩ ይሞታሉ፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በየ1000 በሕይወት ከሚወለዱ ሕፃናት 5 አመት ዕድሜ ሳይሞላቸው የሚሞቱት ሕፃናት ቁጥር 142 እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት የሥነ-ሕዝብ ችግሮች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶባቸው ካልተቀረፉ በስተቀር በሕዝቡ ኑሮ ጥራት ላይና በኢኮኖሚ ልማት ዕድገት ላይ ከፍተኛ ጫና ሊያሳድሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በኀብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል ላይ እንቅፋት ከፈጠሩ ችግሮች ውስጥ አንዱ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በገጠሩ ከፍተኛ ጥግግት ከመኖሩ የተነሣ ኑሮን ለማሸነፍ ሲባል የደን መጨፍጨፍ እንዲበራከት፣ ዳገታማ ቦታዎች እንዲታረሱ ከብቶች ሣርን ከመጠን በላይ እንዲግጡት በማድረግ የአፈር መሸርሸር እንዲበዛ ያደርጋል፡፡ ይህም ደግሞ በበኩሉ መሬት ምርታማነትዋ እንዲቀነስና የአየር መዛባት እንዲከሰት ምክንያት በመሆኑ የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ ሊሸከም የማይችል አካባቢ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

ከጥቂት አስርት አመታት በፊት ከ40% በላይ የነበረው የክልሉ የደን ሽፋን ባሁኑ ጊዜ ወደ 11% መውረዱ የአካባቢ ጥበቃው ሁኔታ በከፍተኛ አደጋ ላይ እንዳለ የሚያመለክት ነው፡፡

ባሁኑ ጊዜ የክልሉ ትምህርት ሴክተር አገልግሎት ፈጣን መሻሻሎችን እያሳየ የመጣ ቢሆንም፣ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከሚያመጣው ጫና የተነሣ በትምህርት አቅርቦትና ጥራት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አድርጓል፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን ያለው የተማሪ መምህርት የተማሪ ክፍል እና የተማሪ መጽሐፍ ጥምርታ መሆን ከነበረበት ጋር ሲነፃፀር ክፍተቱ ትልቅ ነው፡፡

<u>ለምሣሌ፡-</u> በአገር አቀፉ መስፈርት መሠረት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪ መምህርና የተማሪ ክፍል ጥምርታ 1፡50 መሆን ሲገባው በ2000 ዓ.ም የመምህር ተማሪ ጥምርታ በክልላችን 1፡75 እና የክፍል-ተማሪ ጥምርታ ደግሞ 1፡72 በመሆን የትምህርት ጥራቱ ዝቅ እንዲል አስተዋጽኦ አድርጓአል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እንደማንኛውም በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮችና እንደ ሌሎች ኢትዮጵያ ክፍሎች ሁሉ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልልም በርካታ ማኅበራዊ ጠንቆች የተስፋፉበት ነው፡፡ እንደ ዩኒሴፍ የህፃናት መርጃ ድርጅት ጥናታዊ መግለጫ መሠረት በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ከ15 ዓመት በታች ካሉ ሕፃናት መካከል ከአምስቱ አንዱ በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ታውቋል፡፡ የክልሉ ሁኔታ ከዚህ የተለየ አይሆንም፡፡ ለምሣሌ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ በዲላ ፣በአርባምንጭና በሀዋሣ በ50 ሕፃናት ላይ ባደረገው ጥናት መሠረት ወላጅ አልባ ከሆኑት ውስጥ 86% የሚሆኑት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እናቶቻቸውና አባቶቻቸው ወይም አሣዳጊዎቻቸው የሞቱባቸው እንደሆኑ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሥራ አጥነት በክልሉ ካሉ ማኅበራዊ ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የደቡብ ክልል ሥራ አጥነት መጠን 35% እንደደረሰ በ1997 ዓ.ም የተደረገው ጥናት ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም የአረጋዊያንና የአካል ጉዳተኞች ችግሮችም ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በ1989 ዓ.ም በክልሉ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ በተደረገው ጥናት ከተካተቱት አረጋዊያን መካከል 53.3% ምንም መተዳደሪያ የሌላቸውና ከነዚህ ውስጥ ሩብ የሚያህሉት በልመና የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ከፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የተነሣ የአረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች ችግር ሊባባስና ቸል ሊባል ስለሚችል ይህንን ጉዳይ

እንደአንድ የሥነ-ሕዝብ ችግር ተደርጎ በመውሰድ በዕቅድና በስትራቴጂ በተደገፈ ሁኔታ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የጎዳና ተዳዳሪነት ሴተኛ አዳሪነትና ወጣት ጥፋተኝነት በክልሉ የሚገኙ ማኅበራዊ ጠንቆች ናቸው፡፡ እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም በተደረገው በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በክልሉ 3,361 ሴተኛ አዳሪዎች እንደሚገኙ የተቆጠረ ሲሆን ባሁኑ ጊዜ ይህ ቁጥር እጅጉን ከፍ ያለ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ እነዚህ ሴቶች ራሳቸውን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ለአባለዘር በሽታዎች በማጋለጥ ለከፍተኛ ሞትና ሥቃይ እንዲሁም ለሥነ-ልቡና ውድቀት የተዳረጉ ከመሆኑም በላይ በርካታ የማኅበረሰቡ አምራች የሆነው ክፍል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመሳሰሉ ለገዳይና ለአሰቃይ በሽታዎች እንዲጋለጡ መንገድ በመሆን ድህነት በይበልጥ እንዲስፋፋ ምክንያት ሲሆኑ ቆይተዋል፡፡ እንዲሁም ጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት በአገር አቀፍ ደረጃ 100,000 በክልላችን ደግሞ 30,000 (የክልሉ ሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም 1999) እንደሚኖሩ የተገመተ ሲሆን ይህም በየአመቱ 5% እየጨመረ እንደሚሄድ ተገልፆአል፡፡

እነዚህ ሌሎች ማኅበራዊ ጠንቆች ከፈጣን ሕዝብ ቁጥር ዕድገትና ከዝቅተኛ ኢኮኖሚ አቅም ጋር የተያያዘ በመሆኑ የኗሪውን ቁጥርና የኢኮኖሚያውን ደረጃ አጣጥሞ በመሄድ ችግሮችን መቅረፍ ይቻላል፡፡

ሌላው መታለፍ የሌለበት ነጥብ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ነው፡፡ ሴት ልጅ ትምህርት ቤት እንዳትገባ፣ የራሷ ገቢ እንዳይኖራትና በተዋልዶ ጤና መብቶች ላይ እንዳትወስን ተፅዕኖ በተደረገባት ቁጥር የእናቶችና የሕፃናት ሞትና ስቃይ ከመጨመሩም በላይ የውልደት መጠኑ ከፍ እንዲል በማድረግ ከኢኮኖሚው በጣም የቀደመ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እንዲኖር ምክንያት በመሆን የሀገሪቱ የልማት ዕድገት እንዲዘገይ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቃቀሱት የሥነ-ሕዝብ ቁልፍ ጉዳዮች በእያንዳንዱ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ቦታና ትኩረት አግኝተው ካልተተገበሩ በስተቀር የልማት ጥረቶቻቸውን መና ሊያስቀሩ የሚችሉበት አቅም አላቸው፡፡

## *1.5 የሥነ-ሕዝብና ልማት ትስስር ምንነት*

በአለም አቀፍ ደረጃ የሥነ-ሕዝብና ልማት መስተጋብርን አስመልክቶ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ረገድ የ1974 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግሥታት የሥነ-ሕዝብ ጉባዔ (WPC) ያወጣው የአለም የሥነ-ሕዝብ መርሃ -ግብር የመሠረት ድንጋይ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ በዚህ

ስብሰባ ላይ በጉልህ የተንፀባረቀው ሀሳብ <ልማት ከሁሉም የተሻለው የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ ነው> ( Development is the best Contraceptive) የሚለው ነው፡፡ የአለም የሥነ-ሕዝብ መርሐ-ግብር በግልጽ እንዳስቀመጠው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ዋናው አላማ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃና የአኗኗር ዓይነት ጥራት ከፍ ማድረግ ነው፡፡

በጉባዔው መግለጫ የተለያዩ አካላት የተለያየ ትርጉም የሰጡበት ቢሆንም አንድ ግልፅ የሆነ ነገር ቢኖር የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የአጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ዕቅድ አንዱ አካል መሆን ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አባባል የልማት ፖሊሲዎች ውጤት እንዲያስገኙ ከተፈለገ የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራምን አብረው ሊያካትቱ የሚገባቸው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አንፃር ስነ-ሕዝብ በልማት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ በስነ-ሕዝብ ገጽታዎች ይንፀባረቃል፡፡ የሥነ-ሕዝብ ገፅታዎች ተብለው የሚታወቁት የሕዝብ ብዛት (Pop$^n$ Size ) የሕዝብ አወቃቀር (Pop$^n$ Composition )፣ የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ (Pop$^n$ Growth rate) እና የሕዝብ አሰፋፈር (Pop$^n$ distn ) ሲሆኑ እነዚህ ገጽታዎች በየግዜው እንዲለዋወጡ የሚያደርጓቸው ደግሞ ሦስት ምክንያቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ውልደት ( Fertility ) ፣ሞት( Mortality ) እና ፍልሰት( Migration ) ናቸው፡፡

የሥነ-ሕዝብ ገጽታዎች በበኩላቸው የአንድ አገር ወይም ክልል የነፍስ ወከፍ ገቢ ከፍ ወይም ዝቅ እንዲል፣መንግሥት ለዕለታዊ ፍጆታዎችና ለማህበራዊ ተቋማት ግንባታ፣ ለትምህርት፣ጤናና ለሌሎች ማህበራዊ ግልጋሎት የሚያወጣውን በጀት ቁጠባና ኢንቨስትመንት እንዲኖር ወይም እንዳይኖር፣ ግብርና ዋና መተዳደሪያ በሆነባቸው አገሮች ደግሞ የሰውና የመሬት ጥምርታን (Man-land-ratio) ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ የሥራ ዕድል ላይ ተፅዕኖ በማሣደር የገቢ መጠን ከፍና ዝቅ እንዲል ያደርጋሉ፡፡

የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች በልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ይደረጉ ሲባል የአንድን አገር የልማት ግቦች ለማሳካት እንዲቻል የዲሞግራፊያዊና ሶሺዮ- ኢኮኖሚያዊ ገፅታዎች በልማት ዕቅድ ዝግጅት ተካተው እንዲተገበሩና አፈጻጸማቸውም ክትትልና ግምገማ እንዲደረግባቸው ማድረግ ማለት ነው፡፡ የስነ-ሕዝብና ልማት ቅንጅት መሠረት የሚያደርገው ዲሞግራፊያዊ ክስተቶች የሶሾዮ-ኢኮኖሚክ ልማት ላይ እንዲሁም የሶሺዮ-ኢኮኖሚክ ልማት ዲሞግራፊያዊ ክስተቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህንን የሁለትዮሽ ትስስር አለመረዳትና በልማት ዕቅድ ውስጥ አለማካተት ማለት ደግሞ የልማት ዕቅዶች የታለመላቸውን አላማ እንዳያሳኩ ማድረግ ነው፡፡

የስነ-ሕዝብ ጉዳይ በልማት ዕቅድ ውስጥ ማካተት ሲባል የተለያዩ የዲሞግራፊያዊ ባህሪያት በእያንዳንዱ የልማት ዕቅድ ክፍሎች ውስጥ መታየት ፣መተግበርና አፈጻጸማቸው ክትትልና ግምገማ ማድረግን ያካትታል፡፡

## *ስትራቴጂክ ጉዳዮች*

በብሄራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊስ ላይ የተመለከቱትን ግቦችና ዓላማዎች ከዳር ለማድረስ ቅድሚያ ከተሰጡት የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በሚያስፈጽሙ ሴ/ር መ/ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ በማካተት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በሚመለከታቸው ሴ/ር መ/ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት በማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አላስፈላጊ ተጽዕኖ እያሳደሩ ያሉትን የሥነ-ሕዝብ ገጽታዎችን በመለየት ከልማት ዕድገቱ ጋር እንዲጣጣሙ ለማስቻል ነው፡፡

እንደሚታወቀው ክልሉ በአሁኑ ወቅት የሁለተኛውን የአምስት አመት የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ከሚመለከታቸው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አስፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶች ጋር በጋራ በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በኘሮግራም ሰነዱ የተመለከቱትና በሚመለከታቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ መ/ቤቶች ይተገበራሉ ተብለው የሚጠበቁ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች ግልጽና በሚለኩ መልኩ በልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ እየሆኑ አይደለም፡፡ ከዚህ አኳያ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅድ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸው የሥነ-ሕዝብና ልማት ቅንጅት የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀትና አስፈጻሚ መ/ቤቶችም በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤና ክህሎት ማስጨበጥ ወሳኝ በመሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም ከሥነ-ሕዝብና ልማት ቅንጅት ጋር በተያያዘ ትኩረት የሚሹ ስትራቴጂክ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የሚሠሩ አካላት ትብብርና ቅንጅት ዝቅተኛ መሆን፣
- በሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አስፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶች ዘንድ በሥነ-ሕዝብና ልማት ቅንጅት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ አናሣ መሆን ፣
- ሴ/ር መ/ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት እቅዶቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያግዝ የአፈጻጸም ማንዋሎችና መመሪያዎች አለመኖር፣

- የሥነ-ተዋልዶ ጤና ችግር ጎልቶ በሚታይባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችና በተለይም ለሴቶችና ወጣቶች ትኩረት ሰጥቶ ያለመንቀሳቀስ ፣
- የክልሉ ኅብረተሰብ በሥነ-ተዋልዶ ጤና እና ሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ከአለመዳበር የተነሣ በሚፈለገው መልክ ተግባራዊ አለመሆን፣
- የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት በተለይም የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት በበቂ መጠንና ጥራት ያለመስፋፋት ፣
- የሴቶች የትምህርት ተሣትፎ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ዝቅተኛ መሆን
- ሴቶች በኅብረተሰቡ ዘንድ የተሰጣቸው ደረጃ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሣ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ያላቸው ተጠቃሚነት አናሣ መሆን፣
- ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ የሕዝብ ዕድገት መኖር፣
- የተፈጥሮ አካባቢ መራቆትና የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ያለመረጋገጥ፣
- ማይምነት ፣ሥራ አጥነት ወ.ዘ.ተ… መስፋፋትና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መበራከት

## ክፍል ሁለት የስነ-ሕዝብና ልማት ትስስር

### 2.1 ስነ-ሕዝብና ትምህርት

ስነ-ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በተለያዩ የልማት መስኮች ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር እንዲሁም የተለያዩ የልማት መስኮች በስነ-ሕዝብ ላይ የበኩላቸውን ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ እሙን ነው፡፡ ከእነዚህ የተለያዩ የልማት መስኮች ውስጥ አንዱ የትምህርት ልማት ዘርፍ ነው፡፡ ትምህርት ለአንድ አገር ዕድገት ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ የልማት ሥራዎች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በትምህርት ላይ ያለውን ተፅዕኖ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናቶች ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን እንደ ት/ቤቶች ፣መምህራን፣የመማሪያ መፃህፍቶችና ቁሳቁሶች፣ ወዘተ…ያሉ የትምህርት ግብዓቶች ፍላጎት እያደገ ይሄዳል፡፡

በሌላ አገላለጽ  የውልደት መጠን እየጨመረ በሄደ መጠን በትምህርት ግብዓቶች ላይ የሚያሳድረው ጫና በመጨመር ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አገሪቷ ወይም ክልሉ ለትምህርት ዘርፍ የሚያመጣውን ዓመታዊ በጀት በእጅጉ ያንረዋል፣በተማሪዎችና በትምህርት ግብዓቶች መካከል ያለውን ጥምርታም ከፍ እያለ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ አገር ላይ የትምህርት መስክ ከፍተኛ እመርታ ካስመዘገበና የተማረ ማኅበረሰብ ከተፈጠረ ስለቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መረጃና አቅርቦት ያለው ግንዛቤ ስለሚጨምር የውልደት መጠን ይቀንሳል፣ እንዲሁም እናቶች የልጆቻቸውን አመጋገብና ጤንነት ስለሚጠብቁ የሕፃናትና ልጆች ሞት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡ በዚህም መሠረት አነስተኛ የሆነ የውልደትና የህፃናት ሞት በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ኅብረተሰቡ ለመማር ያለው ፍላጎትና አቅም ሲጨምር ከፍተኛ የውልደት መጠንና የሕፃናት ሞት ባለበት ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ ኅብረተሰቡ ለትምህርት ያለው ፍላጎትና አቅም ዝቅተኛ እየሆነ ይመጣል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በደቡብ ክልል የሚስተዋለው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት ሴ/ር ላይ እያሳደረ ያለውን ጫና ለመረዳት ከ1996 እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ያሉትን የ5 አመት የትምህርት ተሣትፎ መረጃዎች በመገምገም የቀረበውን ፅሁፍ እንመለከታለን፡፡

### 2.1.1 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በት/ቤቶች አቅርቦት ላይ ያለው ተፅዕኖ

ትምህርትን በበቂ ሁኔታ ለኅብረተሰቡ ለማዳረስ በመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች ፣በግለሰቦችና በኅብረተሰቡ ተሣትፎ የት/ቤቶች ግንባታ ከዓመት ወደ አመት እየጨመረ ይገኛል፦ ለምሣሌ በ1996 ዓ.ም 162 አፀደ ሕፃናት፣2539 የመጀመሪያ ደረጃና 98 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የነበሩ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ይህ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አድጎ 420፣ 4223 እና 164 ት/ቤቶች እንደቅደም ተከተላቸው ሆኗል። ከትምህርት ቢሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የሚገነቡት ት/ቤቶች ብዛት ከአመት ወደ አመት እየጨመረ ቢመጣም ካለው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ባለመመጣጠኑ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ሙሉ በሙሉ የመማር ዕድል አላገኙም ዕድሉን ያገኙትም ቢሆኑ በአብዛኛው አመቺ የመማሪያ ስፍራ አላቸው ማለት አያስደፍርም።

በመንግሥትና በህብረተሰቡ ተሣትፎ እየተገነቡ ያሉ አዳዲስ ት/ቤቶችን ስታንዳርድ ለመጠበቅና በአስፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎች ለማሟላት  የሚያስፈልገው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ በርካታ ት/ቤቶች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ ካለመሆናቸውም በላይ አንድ ት/ቤት ሊያሟላ የሚገባውን ግብዓት ያላሟሉ ናቸው።

<u>ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በአፀደ ሕፃናት ላይ ያለው ተፅዕኖ</u>

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት ሴ/ር ላይ የሚያሣድረው ተጽዕኖ ጎልቶ የሚንፀባረቀው በአፀደ ሕፃናት ወይም የቅድመ መደበኛ ትምህርት አቅርቦት ላይ ነው።
መንግሥት ባለው ውስን አቅም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት ላይ አተኩሮ የአፀደ ሕፃናት ትምህርትን ለግል ባለሀብቶች በመተው በከተሞች አካባቢ ልጆቹን ከፍሎ ለማስተማር አቅም ካለው የህብረተሰብ ክፍል በስተቀር አብዛኞቹ የገጠር ሕፃናት ቅድመ መደበኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችላቸውን የመሠረታዊ የማንበብ፣የመፃፍ፣ አካባቢያቸውን ከትምህርቱ ጋር የማዛመድ ክህሎታቸው ዝቅ እንዲል አድርጓል። ከትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት በ1996 ዓ.ም ዕድሜያቸው ከ4-6 ከነበረና የአፀደ ሕፃናት ትምህርት ማግኘት ከሚገባቸው 1,225,316 ህፃናት ውስጥ 11,018(1.8%) ወንድ እና 9727(1.6%) ሴት ሕፃናት ብቻ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ደግሞ ከ1,676,965 ህፃናት

መካከል 23,449 (2.4%) ወንድ እና 21,254 (2.1%) ሴት ህፃናት ብቻ የመማር ዕድል አግኝተዋል፡፡

ከ1996 እስከ 2000 ዓ.ም በነበሩበት 5 አመታት የአፀደ ሕፃናት ት/ቤቶች በ0.9% ብቻ ሲያድግ በአንፃሩ ትምህርቱን ማግኘት የሚገባቸው ህፃናት ቁጥር በ12.1% አሻቅቧል፡፡

<u>ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ</u>

<u>የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ (NIR)</u>፡- ዕድሜያቸው 7 አመት ከሆነ ጠቅላላ ህፃናት ውስጥ በትምህርት ዘመኑ የአንደኛ ክፍል ትምህርታቸውን ለመከታተል የተመዘገቡ ህፃናት ተማሪዎችን ብዛት የሚያሣይ ጠቋሚ መለኪያ ነው፡፡

በ1996 ዓ.ም 35.7% የነበረው ንጥር ቅበላ በ2000 ዓ.ም ወደ 88.9% አድጓል፡፡ ከዚህ መረጃ 11.1% ያህል 7 አመት የሞላቸው ህፃናት ወደ ት/ቤት እንዳልመጡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሴቶቹን ንጥር ቅበላ ለይተን ስንመለከት በ1996 ዓ.ም 30.6% የነበረ ሲሆን በ2000 ዓ.ም ወደ 83.5% አድጓል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም 16.5% 7 ዓመት የሞላቸው ሴት ህፃናት የትምህርት ዕድል አላገኙም፡፡

<u>የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሣትፎ (NER)</u> በትምህርት ዘመኑ ዕድሜያቸው በአንደኛ ደረጃ የትምህርት ዕድሜ ክልል (ከ7 እስከ 14 አመት) ካሉት ጠቅላላ ልጆች መካከል የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉትን በመቶኛ የሚያመለክት ጠቋሚ መለኪያ ነው፡፡ ይህ ጠቋሚ መለኪያ የትምህርትን ትሣትፎ በተሻለ መልኩ አመልካች በመሆኑ ለዕውነት የቀረበውን መረጃ ይሰጠናል፡፡ በ1996 ዓ.ም 63.7% የነበረው አጠቃላይ ንጥር ቅበላ በ2000 ዓ.ም ወደ 81.7% ያደገ ሲሆን ባለፉት 5 ዓመታት በአማካይ ዓመታዊ ዕድገቱ 18% ነበር፡፡ የሴቶች ንጥር ቅበላም በ1996 ዓ.ም ከነበረበት 52.8% በ2000 ዓ.ም ወደ 77.1% ያደገ ሲሆን ይህም ከጥቅል ቅበላ በ8.9% ልዩነት ያለውና አማካይ ዓመታዊ ዕድገቱም 10% ነበር፡፡ ምንም እንኳን በትምህርት ተሣትፎ ይህን መሠል ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቢታይም የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት መጨመር በሚያስከትለው የትምህርት ግብዓቶች ዕጥረትና በተለያዩ ሌሎች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ነገር ግን የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ዕድል ያላገኙ ልጆች ቁጥር አሁንም በቀላሉ የማይገመት ከመሆኑም በላይ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ት/ቤት ያልተመለሱ ህፃናት ቁጥር በርካታ ነው፡፡

ለምሣሌ በ1996 ዓ.ም 361,214 ወንድ ልጆችና 404,824 ሴት ልጆች በድምሩ 766,038 ልጆች በተለያዩ ምክንያቶች የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ዕድል አላገኙም፡፡ በ2000 ዓ.ም. ደግሞ 266,183 ወንድ ልጆችና 419,799 ሴት ልጆች በድምሩ 689,982 ልጆች ከት/ቤት ውጪ በመሆናቸው በየጊዜው በፍጥነት እየጨመረ የሚሄደው የሕዝብ ቁጥር በ2008 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ የሚደረገውን ስኬት ይፈታተኑታል፡፡

<u>ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ</u>

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚከናወነው የትምህርት ሥራ በጎም ይሁን መጥፎ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መነሻ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ የተገለፀው አሉታዊ ገፅታዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ጨምረው ወይም ብሰው ይታያሉ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል ዕድሜያቸው ከሚፈቅድላቸው /ከ15-16 ዓመት/ ከሆኑ አጠቃላይ 622070 ልጆች መካከል በ1996 ዓ.ም በጥቅል ተሣትፎ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል የቻሉ 82,228 /26.2% /ወንዶችና 33,488 /10.9% /ሴቶች ሲሆኑ በ2000 ዓ.ም. ደግሞ ከአጠቃላይ 811,596 ልጆች መካከል 154,863 /37.64/ ወንዶችና 76042/19%/ ሴቶች ነበሩ፡፡

ከ1996 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም በነበረው ጊዜ ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርታቸውን መከታተል የሚገባቸው ልጆች ቁጥር በ115,189 ሲጨምር ት/ቤት ገብተው በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ በ189,526 አድጓል፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ1996 ዓ.ም ከነበረበት 18.6% /ወንድ 26.2% እንዲሁም ሴት 10.9%/ በ2000 ዓ.ም ወደ 28.5% /ወንድ 37.6% እና ሴት 19% / ብቻ አድጓል፡፡

በንጥር ቅበላ ሲሰላም በ2000 ዓ.ም 15.4% / ወንድ 19.1%፣ ሴት 11.4%/ ብቻ ይሆናል፡፡፡ ይህም ዕድሜያቸው ከ15-16 ከሆኑ ተማሪዎች መካከል 84.6% / ወንድ 80.9% ሴት 89.6% / የሚሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል አለመቻላቸውን ያስገነዝባል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን መከታተል ያልቻሉ ወጣቶች በሙሉ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ስታንዳርዱን የጠበቀ ት/ቤት ይሠራ ቢባል በጣም ብዙ ት/ቤቶች መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡ ት/ቤቶቹን ለመስራት የሚጠይቀው ወጪ፣ የመምህራን ቁጥር፣ የተለያዩ የትምህርት መሣሪያዎች፣ ወዘተ ለማሟላት የመንግሥትን አቅም ይፈታተናል፡፡

በአጠቃላይ በ1ኛና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችን ብዛት በማነፃፀር መረዳት የሚቻለው የትምህርት ደረጃ ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር የወንዶቹም ሆነ የሴቶች የትምህርት ተሣትፎ እየቀነሰ መሄዱን ነው፡፡ በተለይም የሴቶቹ ከወንዶቹ ጋር ሲነፃፀር በእጥፍና ከዚያ በላይ እንደሚቀንስ ከቀረቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል ለሴት ተማሪዎች የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን መቀጠል አለመቻል የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ ከዚህ ውስጥ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ከአቅም በላይ ልጅ ለመውለድ፣ ለኤች አይ ቪ ኤድስና ፣ለሌሎች የአባላዘር በሽታዎች መጋለጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## *ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት ጥራት አመልካቾች ላይ ያለው ተጽዕኖ በመምህራን ላይ*

*የሕዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የተማሪዎች ቁጥር መጨመርና በተማሪዎቹ ቁጥር አንፃር የመምህራን ቁጥርም እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል ውጤታማ ተማሪዎች ለማፍራት የመምህራን ብቃት ወሳኝ በመሆኑ በየደረጃው ለሚሰጠው ትምህርት ብቃት ያላቸው መምህራንን አሰልጥኖ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡*

*በዚሁ መሠረት ለአንደኛ ደረጃ 1ኛ ሣይክል ከ1-4ኛ ክፍል ቲ.ቲ.አይ ፣ለአንደኛ ደረጃ 2ኛ ሣይክል/ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል/ዲፕሎማ፣ እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲግሪ ያላቸው መምህራኖች ያስፈልጋሉ፡፡*

*በ2000 ዓ/ም ለአንደኛ ደረጃ 1ኛ ሣይክል የነበሩት መምህራን 31,266 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ 99.8% ለደረጃው የሰለጠኑ ነበሩ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሣይክል ደግሞ 13,217 መምህራን የነበሩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 83.4% ለደረጃው የሰለጠኑ ነበሩ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ የነበሩ መምህራን ቁጥር 2328 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 57.17% ብቻ ለደረጃው የሰለጠኑ ነበሩ ከእነዚህ ከትምህርት ቢሮ የተገኙ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው ትምህርትን በጥራት ለመስጠት በመጀመሪያ ደረጃ 2ኛ ሣይክልና በተለይም ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለደረጃው የሚመጥኑ መምህራንን የማሰልጠን ሰፊ ሥራ መኖሩን ነው፡፡*

## *የመምህር ተማሪ ጥምርታ*

*ይህ መለኪያ የሚያመለክተው መምህራን ምን ያህል ተማሪዎቻቸውን በቅርበት አግኝተው ሊረዷቸውና በትምህርት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ሊያቃልሉ ችለዋል? ምን ያህሉንስ ውጤታማ እንዲሆኑ አድርገዋል? የሚለውን ነው፡፡*

በ1996 ዓ.ም. ከ1ኛ-4ኛ ክፍል የነበረው የመምህር ተማሪ ጥምርታ 1:71 ሲሆን በ2000 ዓ/ም 1:75 ሆኗል፡፡ ይህም ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 1:50 በጣም የራቀ ነው፡፡ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ደግሞ በ1996 ዓ.ም. 1:54 የነበረ ሲሆን በ2000 ዓ.ም. ግን 1:64 ደርሷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችም ከ1996 ዓ.ም. እስከ 1999 ዓ.ም. ድረስ አንድ ጊዜ ከፍ ሲል ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ በማለት በ2000 ዓ.ም. 1:56 ሆኗል፡፡

## የክፍል ተማሪ ጥምርታ

በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ የተማሪዎች ቁጥር መያዝ ከሚገባው በላይ ከፍ ባለ መጠን በክፍሉ ውስጥ የተጨናነቀ አየር እንዲኖር በማድረግ፣ በተማሪዎቹም ሆነ በመምህራን ላይ የመጻከም ስሜት በመፍጠር፣ መምህሩ ተማሪዎቹን በክፍል ውስጥ በሚገባ እየተዘዋወረ መከታተልና መደገፍ እንዳይችል በማድረግ፣ ወደ ኋላ የሚቀመጡ ተማሪዎች መምህሩ የሚጽፈውንም ሆነ የሚናገረውን በተገቢው ሁኔታ እንዳይከታተሉ በማድረግ፣ ወ.ዘ.ተ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በ1996 ዓ.ም. በአንደኛ ደረጃ 1ኛ ሣይክል የክፍል ተማሪ ጥምርታ 1:82 የነበረ ሲሆን እየተሻሻለ መጥቶ በ2000 ዓ.ም. 1:72 ደርሷል፡፡ በአንደኛ ደረጃ 2ኛ ሣይክልም በ1996 ዓ.ም. 1:75 የነበረው የክፍል ተማሪዎች ጥምርታ በ2000 ዓ.ም. 1:73 ሆኗል፡፡

ምንም እንኳን በ1996 ዓ/ም የነበረው የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር በ2000 ዓ/ም በ66.3%፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ67.3% ዕድገት ቢያሣዩም በየጊዜው በየደረጃው ባሉ የትምህርት እርከኖች እየጨመረ የሚመጣውን የተማሪዎች ቁጥር ስታንዳርዱን በጠበቀ ሁኔታ ተቀብሎ ለማስተማር አለመቻሉን ይጠቁማል፡፡

## የመጽሐፍ ተማሪ ጥምርታ

የተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን የተለያዩ የትምህርት መጽሐፍቶች ፍላጎት በዛው መጠን እያደገ ይሄዳል፡፡

በ1996 ዓ/ም የነበረውን ሁኔታ የሚያሣይ መረጃ ባይገኝም በ1998 ዓ/ም በክልሉ መንግሥት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ላሏቸው ት/ቤቶች መፃሕፍትን 1:1 ለማዳረስ የተቻለ ቢሆንም በ2000 ዓ/ም በአንደኛ ደረጃ 1ኛ ሣይክል በአማካይ 1:2 በሁለተኛ ሣይክል ደግሞ 1:4 እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በስታንዳርዱ መሠረት ጥምርታውን 1:1 አድርጎ ለማዝለቅ በየጊዜው እየጨመረ በሚመጣው የተማሪ ቁጥር መሠረት ተጨማሪ መፃሕፍቶችን አትሞ ለማውጣት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

**የትምህርት ቴክኖሎጂ አቅርቦት**

መንግሥት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በቴክኖሎጂ እየታገዘ እንዲሰጥ ባደረገው ጥረት ትምህርት በፕላዝማ ቴሌቪዥን መስጠት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል በክልሉ ከሚገኙ 164 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ 101 ት/ቤቶች የፕላዝማ ተከላ የተካሄደላቸው ሲሆን ፕላዝማ ባልተተከለባቸውና ወደፊት አዲስ በሚከፈቱ ት/ቤቶች የትምህርት ቴክኖሎጂ አቅርቦት እጅግ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ይሆናል።

**ሌሎች ግብዓቶች**

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የትምህርት ግብዓቶች ማለትም መምህራን፣ መፃሕፍትና የመማሪያ ክፍሎች በተጨማሪ ላብራቶሪዎች፣ የትምህርት መርጃ ማዕከላት፣ የውሃ፣ የመብራትና የሽንት ቤት አገልግሎቶች፣ የስፖርት ሜዳ ዕቃዎችና የመሳሰሉት እንዲሁም የት/ቤት አስተዳደር ሠራተኞች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ወዘተ ሁሉ በትምህርት ግብዓትነት ይጠቀሳሉ።

ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ እንደላይብረሪ፣ የመሰብሰቢያ አደራሽ፣ ውሃ፣ ክሊኒክ፣ ኤሌክትሪክ፣ ወ.ዘ.ተ ያሉ የትምህርት ግብዓቶች አልተሟሉም። ጥራት ያለውን ትምህርት ለመስጠት መንግሥት ከሰጠው ከፍተኛ ትኩረት አንፃር እነዚህን ግብዓቶች ሟሟላት የማይታለፍ ሥራ ነው።

### 2.1.2 ትምህርት በስነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ

ትምህርት በአንድ አገር ማህበረሰብ ውስጥ የጋብቻ ዕድሜን በማዘግየትና የመውለጃ የዕድሜ ክልል ከ15-49 በማሳጠር፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ዘዴዎችን የማወቅና የመጠቀም ልምድን በማዳበር፣ ሴቶችን በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች የመሰማራትና ተጠቃሚነትን ደረጃ በማጎልበት፣ በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ የውሣኔ ሰጪነት ደረጃን በማሣደግ፣ መሠረታዊ ትምህርት ለሁሉም በሚለው መርህ መሠረት ወላጆች ሁሉንም ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት መላክ ስለሚገደዱና የመማሪያ ወጪያቸውም ከፍ ስለሚል በዚህም ምክንያት ወላጆቻቸውን በስራ ስለማያግዙና ለወላጆቻቸው የሚያስገኙት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ዝቅተኛ ስለሚሆን ወላጆች ልጅ የመውለድ ፍላጎታቸውን እንዲቀንስ ያደርገዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ትምህርት በባልና ሚስት መካከል የመወያየትና የመግባባት ባሕልን በማጎልበት፣ የሚወለዱ የልጆች ብዛት በጋራ እንዲወሰን በማድረግ፣ እናቶች የልጆቻቸውን

አመጋገብና ጤንነት እንዲጠብቁ በማድረግ የሕፃናትና የልጆች ሞት እንዲቀንስና የሚሞቱ ልጆችን ለመተካት ሲባል የሚኖረውን ብዙ ልጆችን የመውለድ ልምድ በማስቀረት፣ እናቶች ከቤት ውጪ በሚገኙ የሥራ መስኮች ላይ የመሰማራት ዕድላቸውን ከፍ በማድረግ ልጆችን ወልዶ ለመንከባከብ በቂ ጊዜ እንዳይኖራቸው በማድረግ፣ ሴቶች  በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስኮች ያላቸውን የውሣኔ ሰጪነት ደረጃ ከፍ በማድረግ የሚወልዱትን የልጅ መጠን በፍላጎታቸው እንዲወስኑ በማድረግ፣ ወላጆች ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ባህላዊ ዕምነቶች ተላቀው አነስተኛ ቤተሰብ ለመፍጠር የሚያስችላቸውን ዕውቀትና ልምድ በማጎልበት፣ ለእናቶች ሕፃናትና ልጆች ሞት መንስኤ የሆኑ ችግሮችን በማስወገድ በሰዎች በተጨናነቁ ቦታዎች በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሰውን ውድመት ከመከላከል አንፃር የተማሩ ሰዎች የተሻለ የሥራ ዕድል ወዳለባቸው አካባቢዎች እንዲሄዱ በማድረግ፣ በባሕሪያቸው ከፍተኛ የሰው ጉልበት ለሚጠቀሙ /Labour intensive/ የማምረቻ ተቋማት ወጪ፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠርና በማስፋፋት በሂደት የውልደት መጠን ደረጃ በደረጃ እንዲቀንስ በማድረግ ፣ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ የትምህርት ተቋማቶች በርካታ ወጣቶች ከገጠር ወደ ከተማ እንዲፈልሱ በማድረግ ወጣቶቹ ገጠር ቢቆዩ ሊኖራቸው ይችል የነበረውን የውልደት መጠን በመቀነስ እንዲሁም ሰዎች በከተማ እንዲኖሩ በማድረግና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤን በመከተል አነስተኛ የቤተሰብ መጠን የመኖር ባህልን በማጎልበት ከገቢ መጠን ጋር የተመጠነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በቤተሰብ ደረጃ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

### 2.1.3 <u>በትምህርት ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች</u>

የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በልማት ዕቅድ ውስጥ በማካተት ሂደት ውስጥ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለብን፡፡

1. በእያንዳንዱ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ውስጥ እንደ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠን፣ የዕድሜና የፆታ ስብጥር፣ወዘተ... ያሉ <u>ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች</u> መካተታቸውን ማረጋገጥ፣
2. ዲሞግራፊያዊ ባህሪያት ሴክተሩ ካለበት የልማት ችግሮች አንዱ ምክንያት መሆናቸውን መገንዘብና እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ደግሞ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ ውስጥ ማካተትና መተግበር አስፈላጊ መሆኑን ማመን ናቸው፡፡

3. ሥነ-ህዝብ ነክ ችግሮች በልማት ዕቅዱ ውስጥ ዓላማ እና ግብ እንዲሁም ይህንን ለማስፈጸም በጀት የተመደበ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

በትምህርት ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች

- የክልሉ ሕዝብ የዕድሜ አወቃቀር የሚያሣይ መረጃ፣
- በመማሪያ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች ብዛት፣
- በክልሉ ውስጥ በመማሪያ ዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች ስርጭታቸውን የሚያሣይ መረጃ፣
- በመማሪያ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በየዓመቱ በምን ያህል መጠን እየጨመሩ እንዳሉ የሚያሣይ መረጃ እና
- በክልሉ ውስጥ ያለውን ወቅታዊ የሕዝቦች ፍልሰት ሁኔታን የሚያሣይ መረጃ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

<u>በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችና ዓመታዊ የዕድገት መጠን መረጃ አስፈላጊነት</u>

በየአመቱ በመጀመሪያ ደረጃ፣በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመማሪያ ዕድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ሰዎችን መረጃ አግኝቶ በዕቅድ ውስጥ ማካተት በየአመቱ በትምህርት ዘርፍ የሚያስፈልጉትን የትምህርት ግብዓቶች መጠን ለማወቅና አስፈላጊውን በጀት ለመመደብ ይረዳል፡፡

<u>በመማሪያ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች መረጃ አጠቃቀም ዘዴ</u>

- የአንድን አካባቢ ወይም ክልል አጠቃላይ ነዋሪ ሕዝብ የዕድሜ አወቃቀር የሚያሣይ መረጃ ማግኘት፣
- የአጠቃላይ ህዝቡን የዕድሜ አወቃቀር ከሚያሣየው መረጃ ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች የመማሪያ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን በሚከተለው ሁኔታ ለይቶ ማስቀመጥ፣
- ዕድሜያቸው ከ3-6 ዓመት በአፀደ ሕፃናት ትምህርት
- ዕደሜአቸው ከ7-10 አመት በመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ ሳይክል ( ከክፍል 1-4)
- ዕድሜያቸው ከ11-14 ዓመት ‹‹ ‹‹ 2ኛ ሳይክል (ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል)
- ዕደሜያቸው ከ15-18ዓመት በከፍተኛ 2ኛ ደ/ት/ቤት (ከ9ኛ-12ኛ) የመማሪያ ዕድሜ ክልል ላይ የሚገኙ መሆናቸውን መረዳትና በዕቅድ ውስጥ በማካተት አስፈላጊ የትምህርት ግብዓቶችን ከዚህ አንፃር ለሚሟላት ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡

## በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ክልላዊ ስርጭታቸውን የሚያሣይ መረጃ ጠቀሜታ

እንደሚታወቀው ሁሉ በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በሁሉም ስፍራ በእኩል መጠን አይገኙም፡፡ ለምሣሌ በደጋማው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ህዝብ በብዛት ተሰባስቦ የሚኖርበት አካባቢ በመሆኑ በአንድ ስኩዌር ኪ.ሜትር ከ600 ሰዎች በላይ ሲኖሩ በቆላማው አካባቢ ደግሞ የሕዝቡ አሠፋፈር የተራራቀ በመሆኑ በአንድ ስከዌር ኪ.ሜትር የሚኖሩ ሰዎች ብዛት ወደ 14 አካባቢ ይደርሳል፡፡

በዚህ መሠረት በደጋማውና በቆላማው የክልላችን አካባቢዎች የሚገኙ በመማሪያ የዕድሜ ክፍል የሚገኙ ልጆች ብዛት የተለያዩ ናቸው ማለት ነው፡፡

በተመሣሣይ መልኩ በከተማ አካባቢ የሚገኙና በገጠር አካባቢ የሚገኙ በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ብዛት የተለያየ ነው፡፡

በመሆኑም ይህንን መረጃ ማግኘትና በሴ/ሩ የልማት ዕቅድ ውስጥ ማካተቱ ምን ያህል ት/ቤቶች በየትኛው የትምህርት ደረጃና ቦታ መገንባት እንዳለባቸው፣ በምን ደረጃ የሠለጠኑ መምህራኖች፣የመማሪያ መጽሐፍቶችና ክፍሎች ወዘተ … እንደሚያስፈልጉ ለመወሰን ይረዳል፡፡

## ወቅታዊ የሕዝቦች ፍልሰት ሁኔታን የሚያሳይ መረጃ ጠቀሜታ

የአንድን አካባቢ ህዝብ ወቅታዊ የሕዝቦች ፍልሰት ሁኔታን የሚያሳይ መረጃ አግኝቶ በልማት ዕቅድ ውስጥ ማካተት ለዛ አካባቢ የሚያስፈልገውን የትምህርት ግብዓቶች አቅርቦት ለመወሰን ይረዳል፡፡

ለምሣሌ ያህል እንደአዋሣ ባሉ ትላልቅ ከተማች ውስጥ በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ብዛት የሚያሣይ መረጃን ብቻ ይዘን በልማት ዕቅዳችን ውስጥ አካተን ብንሰራ በፍልሰት ምክንያት ወደእነዚህ አካባቢዎች የመጡ በርካታ በመማሪያ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና የትምህርት አገልግሎት ማግኘት የሚፈልጉ ልጆች የትምህርቱ ተቋዳሽ እንዳይሆኑና ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

**በትምህርት ሴ/ር የልማት ዕቅድ ውስጥ መካተት የሚገባቸው የተመረጡ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮች**

በክልላችን የሚስተዋለው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በተለይም በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ብዛት ከፍተኛ መሆን የትምህርት አቅርቦትን በስፋትና በጥራት ለኀብረተሰቡ ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት አዳጋች አድርጎታል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ሴ/ር በየአመቱ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን የትምህርት አቅርቦት ፍላጎት ለማርካት ከሚወስዳቸው እርምጃዎች ጎን ለጎን በየአመቱ በከፍተኛ መጠን እያደገ የሚገኘውን በመማሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል የውልደት መጠንን ለመቆጣጠር የሚረዱ የተለያዩ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርበታል፡፡

- ከዚህ አንፃር የሴቶችን የትምህርት ተሣትፎ ከፍ እንዲል የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፣
- በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪ የስነ-ሕዝብና ሥነ-ተዋልዶ ጤና ክበባትን ማቋቋምና ማጠናከር፣
- መሀይምነትን ለማስወገድ እንዲቻል መደበኛ ያልሆኑ ትምህርቶችን ማስፋፋት፣
- የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርትና በተለያዩ ደረጃዎች በሚገኙ የስልጠና ተቋማት ካሪኩለም ውስጥ አካቶ መቅረጽ ፣ ወ.ዘ.ተ... ተማሪዎችና ማኀበረሰቡ ስለ ሥነ-ሕዝብና ተያያዥ ጉዳዮች ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ በማድረግ የውልደት መጠን እየቀነሰ እንዲመጣ ይረዳሉ፡፡

## 2.2 ሥነ-ሕዝብና ጤና

### 2.2.1 ሥነ-ሕዝብ በጤና ላይ ያለው ተፅዕኖ

የሕዝብ ቁጥር እድገት ፣ለውጥ ፣የእድሜ ስብጥርና የአሠፋፈር ሁኔታ የጤናን ጨምሮ የአገልግሎቶችን ሥርጭትና ፍላጎት በእጅጉ ይወስናል፡፡ ይህም የሚሆነው የመሠረተ ልማት ግንባታ በተመጠነ ፍጥነት በሚያድግበት ሁኔታ በከፍተኛ ፍጥነት በሚያድገው ህዝብ ቁጥር ልክ ማስፋፋት ስለማይችል ነው፡፡ በአንድ ሀገር ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ሲኖር የጤና አገልግሎት የሚፈልገውን ህዝብ በመጨመር የአገልግሎት ማስፋፋትን የግድ የሚል ይሆናል፡፡

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት የኅብረተሰቡን የጤና ሁኔታ የሚወስንበት የተለያዩ ማሳያዎች አሉት፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በማኅበረሰብ ላይ የሚያመጣውን ተጽእኖ ለመጠቃቀስ ያህልም፡፡

- ሳይራራቁ የተወለዱ ልጆች ከፍተኛ ለሆነ ሞት ይጋለጣሉ፡
- አራርቆ በመውለድ በአራት ወሊድ ውስጥ አንድ ሕፃን መውለድን ያስቀራል፡፡
- ለመውለድ እድሜ ካልደረሰች እናት የተወለደ ሕፃን የመሞት እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት እናቶችን በሕክምና ካልተደገፈ ውርጃ በመከላከል የእናቶችን ሞት ይቀንሳል፣
- ቤተሰብ ምጣኔ 25% የሚሆነውን የእናቶችን ሞት ይቀንሣል፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ውጤቶች ማግኘት የሚቻለው ግን የጤና አገልግሎቶች ባለው ህዝብ ፍላጎትና ብዛት ልክ ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል ጤና ከሥነ-ሕዝብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው የልማት ሴክተሮች ውስጥ አንዱ የሆነው፡፡
በመሆኑም የክልሉ ጤና ቢሮ ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር ይህንን ዘርፈ ብዙ የሆነ የጤና ችግር ለመቅረፍ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ አሁንም እያከናወነ ይገኛል፡፡ እንደምሳሌነት ከሚጠቀሱ በርካታ ተግባራት ውስጥ አንዳንዱቹን ለመጥቀስ ያህል በ2000 ዓ.ም በክልሉ ጤና ቢሮ በወጣው ሪፖርት መሠረት በ1986 ዓ.ም. 28 ከመቶው የነበረውን የጤና አገልግሎት በ2000 ዓ.ም ወደ 80% ሊያድግ ችሏል፡፡
ምንም እንኳን በዘርፉ ያለውን የጤና መሠረታዊ ችግር ለመፍታት መንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች የጋራ ርብርብ ቢያደርጉም በክልሉ ውስጥ ፈጣን የሕዝብ እድገት በመኖሩ ምክንያት የጤና ችግር አሁንም ዋነኛው የክልሉ ችግር ሆኗል፡፡ ዓመታዊ የስታትስቲክስ መጽሔት (1999 ዓ.ም) እንደሚያሣየው ክልሉ ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል በመቀጠል ሶስተኛውን ደረጃ ይዞ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር የሚገኝበት ነው፡፡ እንደ መጽሔቱ ገለፃ በክልሉ በ1999 ዓ.ም 15,042,531 ህዝብ ሲገኝ ይህም ህዝብ በአመት 2.9% በመቶ እያደገ ይገኛል፡፡ ይህ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ የሕዝብ ቁጥር በየአመቱ በተወሰነ መልኩ እያደገ በሚመጣ የጤና አገልግሎት ማስፋፋት ላይ ጫና እየፈጠረ መጥቷል፡፡
ይህን እውነታ ለማመልከት የሚያስችል የክልሉ የጤና ቢሮ ባወጣው ሪፖርት መሠረት የጤና ተቋማት የአገልግሎት አቅርቦት ፍላጎት በንጽጽር ሲታይ በብሄራዊ ደረጃ ያለው ስታ ንዳርድ የሚያመለክተው አንድ የገጠር ሆስፒታል ማገልገል ያለበት ለ250,000 ሕዝብ ሲሆን

በክልሉ ግን አንድ የገጠር ሆስፒታል ለ714,288 ሰዎች ያገለግላል፡፡ ይህም በግልና በመያዶች የተሠሩትን ጨምሮ በክልሉ ውስጥ በተገነቡትና አገልግሎት በመስጠት ላይ በሚገኙት 21 ሆስፒታሎች ነው፡፡ በተመሣሣይም አንድ ሪፈራል ሆስፒታል ለአንድ ሚሊዮን ህዝብ ብቻ የሪፈራል አገልግሎት መስጠት ሲጠበቅበት በክልላችን ያለው ብቸኛ ሪፈራል ሆስፒታል የክልሉን ጠቅላላ ህዝብ ለማገልገል ተገዷል፡፡ በዚህም ምክንያት በሆስፒታሎች የአሠራር ደረጃ ጥናትና ብቃት ላይ ምን ያህል እንከን እንደሚፈጥር አያጠያይቅም፡፡

በክልሉ ጤና ቢሮ የ2000 ዓ.ም ሪፖርት መሠረት በክልሉ ውስጥ 169 ጤና ጣቢያዎች ሲገኙ አንድ ጤና ጣቢያም 25,000 ሰው ማስተናገድ ሲኖርበት ያለው ነባራዊ ሁኔታ የሚያሣየው ግን አንድ ጤና ጣቢያ ለ89008 ሰዎች በማገልገል ላይ እንደሚኝ ነው፡፡ ይህም ከወጣው ስታንዳርድ ከሶስት እጥፍ በላይ መሆኑ ነው፡፡ በጤና ኬላ በኩል ስታንዳርዱ አንድ ጤና ኬላ 5,000 ሰው ማስተናገድ ሲኖርበት በአሁኑ ወቅት 5,165 ሰዎችን እያስተናገደ ይገኛል፡፡

የህክምና ባለሙያዎችን በተመለከተ ያለው ጫና ከጤና ተቋማቱ የሚመሳሰል ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣው ስታንዳርድ እንደሚያሣየው አንድ የሕክምና ዶክተር ለ10,000 ህዝብ ሲሆን በክልሉ የ2000 ዓ.ም ሪፖርት መሠረት ግን በክልሉ ያሉ 116 ዶክተሮች እያንዳንዳቸው ለ129,235 ያህል ሕዝብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በነርሶች፣ጤና ኬላዎች ፣ጤና ተቆጣጣሪዎች ላቦራቶሪ ቴክኒሽያኖችና በፋርማሲስቶች በኩልም ያለው ጫና ከዶክተሮቹ ተመሣሣይ መልክ አለው፡፡ ይህም ከመሠረተ ልማቱ በተጨማሪ በጤና ባለሙያዎች ላይም ጫና ከመፍጠሩ አንፃር አብዛኛው ኅብረተሰብ ጥራት ያለው ህክምና እንዳያገኝ እንቅፋት ሆኗል፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ዘርፈ-ብዙ የጤና ተቋማት ከፍላጎት አንፃር ያለው የአቅርቦት ችግርና የጤና ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ባለመሟላት ምክንያት በክልሉ ያለው የእናቶችና ሕፃናት ሞት ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም በወጣው የዲሞግራፊና የጤና ናሙና የጥናት ውጤት መሠረት ክልሉ ከአማራና ጋምቤላ ክልሎች በመቀጠል በከፍተኛ ደረጃ ከአንድ አመት በታች ያሉ ሕፃናት ሞት የሚከሰትበት መሆኑን ያሳያል፡፡ ከአምስት አመት በታች ባሉ ሕፃናት ሞትም ክልሉ 142/1000 የሆነ የሕፃናት ሞት ይታይበታል፡፡ በተመሣሣይ መረጃም የእናቶች ጤናን በተመለከተ በክልሉ 25.3% ብቻ በጤና ተቋማት

የወሊድ አገልግሎት ሲያገኙ ቀሪዎቹ ወደ 75% የሚጠጉት እናቶች ግን ንጽህናው ባልተጠበቀና በቂ የማዋለጃ መሣሪያ በማይገኝበት በቤታቸው ወይንም በልምድ አዋላጆች ይገላገላሉ፡፡ ይህም የሚያሣየው በክልሉ ውስጥ ምን ያህል እናቶች በወሊድ ላይ ለሚከሰት ሞት እንዲሁም እንደ ፊስቱላ ላሉ ተመሣሣይ በሽታዎች መጋለጣቸውን ነው፡፡

በክልሉ ውስጥ ካሉ እርጉዝ እናቶች ውስጥ ቅድመ ወሊድ አገልግሎት የሚያገኙት 30% ብቻ በመሆናቸው ከወሊድ በፊት፣ በወሊድ ጊዜና ከወሊድ በኂላ የሚሞቱ እናቶችን ቁጥር እንዲያሻቅብ አድርጎታል፡፡ እ.ኤ.አ በ2005 የወጣው የዲሞግራፊና ጤና ናሙና ጥናት ውጤት መሠረት በክልሉ ከአንድ መቶ ሺህ እናቶች ውስጥ 673 ያህሉ ከወልድ ጋርተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ይሞታሉ፡፡
እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት እውነታዎች የተከሰቱት ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ከመኖሩ አንፃር ያለውን የጤና መሠረተ ልማት አገልግሎት ባለው ህዝብ ልክ ማመጣጠን አለመቻሉን ባለመቻሉ ነው፡፡ ምንም እንኳን የክልሉ መንግሥት  ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በመሆን የጤና ፖሊሲ ቀርያና ሌሎች ስትራቴጂዎችን ነድፎ የክልሉን የጤና ችግር ለመቅረፍ ርብርብ እያደረገ ቢሆንም አሁንም ግን በጤና በኩል ብዙ መሠራት እንዳለበት የሚያሣይ አመላካቾች ብዙ ናቸው ፡፡

በመሆኑም መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች የልማት አጋሮች ሕዝብ በጤና አገልግሎት ላይ የሚያመጣውን ከፍተኛ ተፅእኖ መቀነስ የሚያስችሉ ሥልቶችን በእቅዶቻቸው ውስጥ አካተው መተግበር እንደሚኖርባቸው የግድ ይላል ፡፡

2.2.2. <u>ጤና በሥነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ</u>

ልማትን በተፋጠነ መልኩ ለማስኬድና የታለመውን የልማት የግብ ስኬት ከግቡ ለማድረስ ለአንዲት ሀገር ካላት የተፈጥሮ ሀብት በተጨማሪም በዋነኛነት ጤናማና ለሥራ ተነሣሽነት ያለው ብቁ ዜጋ ለማፋራትም የጤና ተቋማት በጥራትና በብቃት ማዳረስ ዋነኛው ነጥብ ነው፡፡ የጤና አገልግሎቶች በበቂና በጥራት መኖራቸው የህዝብ ቁጥሩን በመቀነስ የእድሜ ስብጥሩን በማቀራረብ በሥነ-ሕዝብ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው፡፡  ይህም በጤና ብቁ የሆነ ዜጋን በማፍራት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የጤና ተቋማትና አገልግሎቶች በበቂና በጥራት ላለው ህዝብ መዳረሳቸው የሥነ-ሕዝብን ችግሮች ከመፍታት አንፃር  የሚከተሉት ውጤቶች ይኖሩታል፡፡

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ስለሚኖር የውልደት መጠንን በመቀነስ፣
- አራርቆ መውለድ በማስቻል የእናቶችና ህፃናት ሞትን በመቀነስ፣
- በጤና አገልግሎት መስፋፋት ምክንያት የቅድመ ወሊድ፣የወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ስለሚገኝ የእናቶችን ሞት በመቀነስ የቤተሰብን ደህንነት ያቀዳጃል፡፡
- የውልደት መጠናቸው ከፍተኛ የሆኑት ወጣት ክፍሎች ወጣት ተኮር የሆነ የጤናና የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ማግኘት ስለሚችሉ የወሊድ መጠን በወጣቱ በኩል መቆጣጠር ያስችላል፡፡
- ኤች.አይ.ቪና ሌሎችንም የአባላዘር በሽታዎችን በመቆጣጠር ጤናማና ብቁ ዜጋን ማፍራት ያስችላል፡፡
- የማኀበረሰቡን የአመጋገብ የጤናና የንጽህና አጠባበቅ ሥርዓት በማሻሻል የእድሜ ጣራን ከፍ ማድረግ ያስችላል፣ በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጤና የሥነ-ሕዝብ አመልካቾችን የማሣደግ የማሳነስና የመቆጣጠርን ከፍተኛ ሚና በመጫወት የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን እድገት ለማፋጠን ይረዳል፡፡

የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በጤና ሴክተር ዕቅድ ውስጥ በማካተት ሂደት ውስጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1ኛ/ የሥነ-ሕዝብ ተለዋዋጭ ባህሪያት የሚባሉት የውልደት መጠን፣የሞት መጠንና ስደት ከጤና ሴክተር ጋር ያላቸውን ትስስር መተንተንና እነዚህ ባህርያት በሴክተሩ ዕቅድ ውስጥ ማካተት ፣

2ኛ/ እያንዳንዱ የሴክተር ዕቅድ በሚታቀድበት ጊዜ ሴክተሩን የሚመለከቱ ዲሞግራፊያዊ መረጃዎችን መተንተን እቅዱም በመረጃ ላይ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ ፣

በጤና ሴክተር ዕቅድ ውስጥ ለዕቅድ ዝግጅት የሚያስፈልጉ ዲሞግራፊያዊ መረጃዎች

➢ አጠቃላይ መረጃዎች

  - የክልሉ ሕዝብ ቁጥር በእድሜና በፆታ ተለይቶ
  - በመውለድ ደረጃ የሚገኙ ከ15-49 ድረስ ያሉ ሴቶች ቁጥር
  - ከአንድ አመት በታች ያሉ ህፃናት ቁጥር
  - ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናት ቁጥር

➢ ነባራዊ መረጃዎች

- የክልሉ የእናቶች ሞት መጠን በመቶሽኛ
- የክልሉ የጨቅላህፃናትና የልጆች ሞት መጠን በሽኛ
- የክትባት፣የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ፣የቅድመ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድና የወሊድ አገልግሎት ሽፋኖች
- የኤች.አይ.ቪ. ሥርጭት መጠን
- የውልደት መጠን
- ያልተሟላ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ፍላጐት

2.2.3 <u>በጤና ሴ/ር የልማት ዕቅድ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች፣</u>

የጤና ሴክተር እቅዶችን በምናቅድበት ወቅት ትኩረት ሊሠጣቸው የሚገቡ ጠቃሚ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች ውስጥ በዋነኛነት መጠነ ውልደት ፣እና ከእርሱ ጋር ጐን ለጐን የሚከሰተውን ከፍተኛ የህዝብ እድገት፣(የእድሜ ፣ፆታ ስብጥር በተለይም ደግሞ በመውለድ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች) መጠነ ሞት እና ስደት ናቸው፡፡ ስነ-ሕዝብ ነክ ችግሮችን ፈቺ የሆኑ የጤና እቅዶችን ለማቀድ እነዚህን ሶስት መሠረታዊ ቫሪያብሎች መዳሰስ የግድ ይላል፡፡

<u>የውልደት መጠንን የሚያሣይ መረጃ ጠቀሜታ</u>

መጠነ ውልደት የአንድን ክልል ሕዝብ ቁጥር ከፍ በማድረግ ፣የህፃናትን ሞት በመጨመርና በመቀነስ እንዲሁም የእናቶችን ህመምና ሞት በመቆጣጠር ካሉት የሥነ-ሕዝብ አመልካቾች ውስጥ መሪውን ሚና ይይዛል፡፡ በክልሉ ውስጥ ያለው የ5.6 ልጆች የውልደት መጠን የክልሉን ሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር ረገድ የራሱ ሚና አለው ፡፡ ከፍተኛ የወሊድ መጠን የህዝብ ቁጥርን ከመጨመሩም በላይ የእናቶችና የህፃናትን ሞት በመጨመር ከጤና መሠረተ ልማቶች አለመሟላት ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡ ስለዚህ የጤና ሴክተር እቅዶች ከመታቀዳቸው በፊት በክልሉ ውስጥ ስላለው መጠነ ውልደት ሁኔታ ግንዛቤ ማግኘትና መጠነ ውልደቱንም ለመቀነስ መወሰን ቀዳሚው ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ የመጠነ ውልደትን ሁኔታ ስናይ አያይዘን ማየት ያለብን ጉዳይ በመውለድ ክልል ውስጥ ያሉትን ሴቶች ቁጥር ነው፡፡ ይህን ቁጥር ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር ለይተን ማወቃችን ለሥነ ተዋልዶ ጤናና ቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ያለውን ፍላጎት ከሚያሣይ በላይ የውልደት መጠንን ለመገደብም የራሱን ሚና መጫወት ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው ፆታና እድሜ ውስን የሆኑ እቅዶችን ለማቀድ በማስቻል ነው፡፡ መጠነ ውልደት ከፍተኛ ከሆነ ለተወለዱት

ህፃናት የጤና አገልግሎትን ማሟላት ማስፈለጉ ብቻ ሣይሆን በረጅም ጊዜ ለመውሰድ ከፍተኛ እድል ያላቸውን ወንድና ሴት ልጆችን መተካቱ ነው፡፡

- <u>መጠነ ሞት</u> ( Mortality )

መጠነ ሞት ሲባል የማኅበረሰቡን የዕድሜ ጣሪያና የህፃናትና ጨቅላዎችን እንዲሁም እናቶችን ሞት ያጠቃልላል፡፡ ይህ አመልካች የክልሉን አጠቃላይ የሥነ-ሕዝብ የለውጥ ሁኔታ በመቆጣጠር ረገድ ልክ እንደ መጠነ ውልደት ሁሉ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል፡፡ በመሆኑም የጤና ሴክተር እቅዶች በሚታቀድበት ወቅት በእናቶች በሕፃናትና በጨቅላዎች ላይ ያለውን ሞት እና ህመም በመቀነስ ትኩረት በመስጠት መሆን ይገባል፡፡ ሞትን ከመቀነስ በላይ የሕዝቡን የእድሜ ጣሪያም ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል ይገባል፡፡ ይህም የሚሆነው የሕዝቡን የአኗኗር የአመጋገብ ሁኔታ እና ንጽህና እንዲሻሻል ለማድረግ ነው፡፡ የውልደትን መጠን ከመቀነስ ጐን ለጐን መጠነ ሞትን መቀነስ የተቀናጀ ልማት ለማምጣት የሚደረገውን ርብርብ ለማገዝ የሚያስችል ጤናማ፣ ረጅም ዕድሜ ያለውና ብቁ ዜጋ ለመፍጠር ያስችላል፡፡

- <u>ፍልሰት</u>

ከከተማ ገጠር እንዲሁም ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ስደት የሥነ-ሕዝብ ለውጥን በማምጣት ረገድ የራሱ ሚና አለው፡፡ ይህም በከተሞችም ሆነ በገጠር መሠረተ ልማት ላይ ተጽእኖ ያመጣል፡፡ በዚህም ረገድ ከሌላ ቦታ በስደት የሚመጣውን ተቀብሎ መሠረታዊ ልማት ለማሟላት ተሰዶ የሚሄደውን ደግሞ የግፊቱን ሁኔታ ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራት በጤናም ሆነ ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ሴክተሮች የልማት እቅድ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡

በጤና በኩል ስናየው ይህ ስደት የጤና ሴክተር ላይ የራሱን ጫና እንደሚያሣርፍ እሙን ነው፡፡ ከፍተኛ ፍልሰት በሚኖርባቸው የገጠር አካባቢዎች የጤና መሠረት ልማቶችን ማስፋፋት በተቻለ በጤና በኩል የሚመጡ ፍልሰቶችን መከላከል ያስችላል፡፡ ይህም የሚሆነው ሆስፒታሎችን፣ ጤና ጣቢያዎችን ፣ክሊኒኮችን በመገንባትና ለእነሱም የሚሆን በቂ የሰው ሃይልና የማቴሪያል አቅርቦትን በማሟላት ነው፡፡

በአጠቃላይ በጤና ሴ/ር በኩል የሥነ-ሕዝብ ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ የሚጠበቁ ተግባራትን ማከናወን ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራትም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

<u>የውልደት መጠንን መገደብ</u>

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በምርጫና በበቂ ሁኔታ ለሁሉም ስፍራ እንዲዳረስ በማስቻል ለአጠቃቀሙም አስፈላጊውን ቅስቀሳና ትምህርት ማካሄድ
- ለወሊድ የደረሱ ሴቶች ተገቢውን የጤናና አራርቆ መውለድ ትምህርት የሚያገኙበትና ራሳቸውን ማጐልበት የሚያስችላቸውን ወጣት ተኮር የሆኑ የጤናና የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ማስፋፋት
- ወንዶችን የቤተሰብ አገልግሎት አካል የሚያደርጋቸውን የትምህርትና የስልጠና አገልግሎት ማስፋፋት፣
- በጤና ተቋማት ያለውን የውልደት መጠን የህፃናት ቁጥርና የመሣሰሉትን መረጃዎች በበቂ ሁኔታ አደራጅቶ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ
- ለቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት የሚውል በቂ በጀት መመደብና ኅብረተሰቡም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቱን በምርጫው ማግኘቱን ማረጋገጥ
- የማኅበረሰብ ውይይቶችን በመጠቀምና ፣ሞዴል ቤተሰቦችን በማበርታታት እንዲሁም በጎ መልእክተኞችን በማስተባበር ፈጣን የሕዝብ እድገት ሊያመጣ የሚችለውን የውልደት መጠን መገደብ፣

**የሞት መጠንን ለመቀነስ**

- ከፍተኛ የሆነውን የእናቶችና የህፃናትን ህመምና ሞት በክልሉ በከፍተኛ ደረጃ መኖሩ ይታወቃል ። ይህንን ለመቀነስ የሚያስችሉ የቅድመ ወሊድ፡-ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ እንዲዳረስ በማስቻል ፣
- የኤች.አይ.ቪና ሌሎች አባላዘር በሽታዎችን ሥርጭት መቆጣጠር የሚያስችሉ ትምህርት ስልጠናና ሌሎች የጤና አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ ማዳረስ ፣
- ህፃናትንና እናቶችን ለሞት የማያጋልጡ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ኅብረተሰቡ በራሱ እንዲያወግዛቸው የሚያስችሉ የኅብረተሰብ ውይይቶችን ማካሄድ ፣

## 2.3 ስነ-ሕዝብ ግብርናና አካባቢ ጥበቃ

### 2.3.1 ስነ-ሕዝብ በግብርናና አካባቢ ጥበቃ ላይ ያለው ተጽእኖ

መረጃዎችን እንደሚጠቁሙት ከክልሉ ጠቅላላ ሕዝብ 92 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን ዋናው የኑሮ መተዳደሪያውም የግብርናው ዘርፍ ነው። ይህም ማለት የክልሉ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው። በመሆኑም ከክልሉ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርት መጠን (RGDP) ውስጥ የግብርናው ዘርፍ ድርሻ በአማካይ 64 በመቶ

እንደሆነ የሚገመት ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከ82 በመቶ በላይ የሚሆነው ከሰብልና ከእንስሳት ተዋጽኦ እንደሚሸፈን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
የክልሉን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር በማጣጣም ዘላቂ ልማት ዕውን ለማድረግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየተሠራባቸው ከሚገኙት የልማት ኘሮግራሞች አንዱ የግብርና ልማትንና የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በማፋጠን የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ከማረጋገጥ ባሻገር የግብርናው ዘርፍ ለእንዱስትሪው ዕድገት ዋና መሠረት እንዲሆን ዘርፈ-ብዙ ርብርቦሽ እያደረገ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ በፍጥነት እያደገ የሚገኘው የክልሉ ሕዝብ ቁጥር ዕድገት በግብርናው ልማትና አካባቢ ጥበቃ ላይ እየተከናወኑ ያሉትን መጠነ ሰፊ ተግባራትን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተነ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ባለው ክፍል የክልሉ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና ባሕርያት በግብርና ልማትና አካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ላይ እያሳደረ የሚገኘውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

በደቡቡ ክልል ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ እየተከሰቱ ካሉት ችግሮች አንዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ በቤተሰብ ደረጃ ያለው የመሬት ይዞታ እያነሰ መሄድ ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ ካሉ አርሶ አደሮች 10 በመቶ 0.1 ሄክታር ፣46 ከመቶ ከግማሽ ሄክታር በታች፣ 26 ከመቶ ከግማሽ ሄክታር እስከ አንድ ሄክታር እና 4 በመቶ የሚሆነው ከሁለት ሄክታር በላይ የመሬት ይዞታ ይዘው እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ በመሆኑ ምክንያት አብዛኛው አርሶ አደር በአመት የሚያመርተው ምርት እራሱንና ቤተሰቡን ለመመገብ ስለማይበቃው ለከፍተኛ የምግብ ዋስትና ችግር ተጋልጦ ይገኛል፡፡

ከሥነ-ሕዝብ ባህሪያት ጋር በተያያዘም በግብርናውና አካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ላይ አሉታዊ ጫና በማሣደር የሚታወቀው የሕዝብ ሥርጭትና ጥግግት ነው፡፡ በመሆኑም 70% የሚሆነው ሕዝብ የሚኖረው በ42% የክልሉ የቆዳ ስፋት በሆነው በደጋማና ወይና ደጋ አካባቢዎች ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎች የሕዝብ ጥግግቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የክልሉ ግርድፍ የሕዝብ ጥግግት 142 ሰው በካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን የእርሻ መሬት ጥግግት ደግሞ 9.8 ሚጋ ሰዎች በአንድ ሄክታር ነው፡፡

በደቡብ ክልል በማዕከላዊና በሰሜንና ምሥራቅ ዞኖች ማለትም በወላይታ፣በከምባታ ጠምባሮ፣በሃዲያ፣በጉራጌ፣በጌዲኦ እና ሲዳማ ዞኖች ከሚታየው የእርሻ መሬት ጥበት የተነሣ በአንድ ሄክታር ከ22-79 ሰዎች ሰፍረው እንደሚገኙ ከክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ሴ/ር የሚወጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በፍጥነት እያደገ ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር በተያያዘ የምግብ ዋስትና ችግር ጎልቶ ከሚታይባቸው የሀገራችን ክልሎች አንዱ የደቡብ ክልል ሲሆን ከ79 በላይ በሆኑ ወረዳዎች በገጠሩ አካባቢ ብቻ 1.9 ሚሊዮን ህዝብ በየዓመቱ የችግሩ ተጋላጭ ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ 70% ያህሉ ዓመታዊ ምርትና ገቢያቸው እስከ 6ወራት ብቻ ያለውን የምግብ ፍጆታውን የሚሸፍን ሲሆን ቀሪዎቹ በድርቅና ሌሎች መሰል አደጋዎች ሲከሰቱ ለአንድ የምርት ዘመን እንኳን ራሳቸውን ማቋቋም የማይችሉ መሆናቸውን የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ሴ/ር ዓመታዊ ሪፖርት ያመለክታል፡፡ ለምግብ እህል እጦት ዋና ምክንያት ደግሞ ዕድገቱ ፈጣን የሆነ የህዝብ ብዛት ያስከተለው የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ፣የመሬት ይዞታ እጅግ አናሣ መሆን፣የመሬት ለምነት መዳከም፣ምርትና ምርታማነት ማነስ ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከሌሎች በርካታ ምክንያቶች ጋር ተዳምሮ በክልሉ ተፈጥሮ አካባቢ ላይ ከፍተኛ ጫና እያስከተለ ይገኛል፡፡ በዚህም የተነሣ በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከሀገራችን ቆዳ ስፋት 42% ይጠጋ የነበረው የደን ሽፋን በዓይነትና በመጠኑ እየቀነሰ መጥቶ በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ በየአመቱ ከ150,000-200,000 ሄ/ር መሬት እየተጨፈጨፈ ወደ 2.7% ደርሷል፡፡ ክልሉ ከሀገሪቱ አንፃር የተሻለ የተፈጥሮ ደን ሽፋን ያለው ቢሆንም ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ፍጥነት እየተመነጠረ ይገኛል፡፡ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ የጥፋቱ ሂደት ካልተገታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀሪውን ደን ጨርሶ እንደሚጠፋና አሁን ካለንበት የሽፋን መጠን እንደሚቀንስ ይገመታል፡፡

የደን መመንጠር፣የአፈር መከላትና ሌሎችም የተፈጥሮ ሀብቶች መራቆትን በሚመለከት የክልላችንም ተጨባጭ ሁኔታ በአሣሣቢ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም በየአመቱ 180000 ሄ/ር መሬት ደን ይቆረጣል፣ 127 ሚሊዮን ቶን አፈር በየአመቱ ይሸረሸራል፣ ከ80-90 ቶን አፈር ከአንድ ሄ/ር ማሣ ላይ ታጥቦ/ተጠርጎ ይሄዳል፡፡ የመሬት ተዳፋትነትን ችግር ያላገናዘበ እርሻን በማስፋፋት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ የሆነ የአፈር ሀብት መከላትን በማባባስ የምግብ እጥረትና ድህነትን በማስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡

ከፍ ብለው የተጠቀሱትን የተፈጥሮ ሀብት ውድመትንና በረሃማነትን እንዲስፋፋ ያደረገው ደግሞ ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር እየተከሰተ ያለው ከፍተኛ የሆነ የማገዶ ፍላጎት መጨመር ፣ለቤት መስሪያና ለቤት ውሰጥ ቁሣቁስ መስሪያነት የሚያስፈልገው የደን ውጤት ፍላጎት በከፍተኛ ፍጥነት መጨመር ፣እየጨመረ ለመጣው የህዝብ ቁጥር የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል ያሉትን ጥብቅ ደኖች በመመንጠርና በማቃጠል የእርሻ መሬትን ማስፋፋት ፣በንብረተሰቡ ዘንድ በሚቆረጡ ዛፎች ምትክ ሌላ የዛፍ ችግኝ በማፍላት የሚደረግ የዛፍ ተከላ ባሕል እጅግ አነስተኛ መሆኑ፣ ቀደም ሲል በደን ተሸፍነው በነበሩ አካባቢዎች የነበረው ደን ከተመነጠረ በኋላ በአጭር ጊዜ ሊተካ የማይችል ለም አፈር እየተሸረሸረ ለከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ውድመት መደረጉ ከሚጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 2.3.2 ግብርናና አካባቢ ጥበቃ ልማት በሥነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተጽእኖ

በርካታ በሥነ-ሕዝብ ልማት ዙሪያ የተደረጉ ጥናታዊ ሥራዎች እንደሚያመለክቱት ሕዝብና ልማት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደሆኑ ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ማለት አንዱ በሌላው ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለ ነው፡፡ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን እውን ማድረግ የአንድን አካባቢ ሕዝብ ሁለንተናዊ ልማትን በማፋጠን የሕዝቡን የሥራ ባሕልና አመለካከት እንዲዘምን በማድረግ የሥነ-ሕዝብን ገጽታ ማለትም የሕዝብ ቁጥርን፣የዕድሜና የፆታ አወቃቀርን ሁኔታ ከመለወጡም ባሻገር ፈጣን የሕዝብ ቁጥርን ትርጉም ባለ መልኩ ለማርገብ አዎንታዊ ሚና እንደሚያበረክት በዘርፉ የተደረጉ ጥናታዊ ሥራዎች ያመለክታሉ፡፡

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት በተቃራኒ በክልላችን ለሚስተዋለው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ዋነኛ ምክንያት ድህንነትና ከድህነት ጋር የተያያዙ ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ሲሆኑ ለአብነት የሚጠቀሱትም ኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ፣ባህላዊና ኋላ ቀር የውሃና የአፈር አጠባበቅ ዘዴ ፣የተበጣጠሰና አነስተኛ መሬት፣ከግብርና ውጭ የሚሠማሩበት የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ውስንነት ፣የቁጠባ ባህል አለመዳበር ፣የግብርና ግብዓቶች በብቃትና በጥራት አለመሟላት ፣መሠረተ ልማቶች በገጠሩ አካባቢ በስፋት አለመዳረስ፣በዝናብ ላይ ጥገኛ መሆን ፣በቂ ክህሎትና ግንዛቤ አለመኖር ናቸው፡፡

በመሆኑም የግብርናና የአካባቢ ጥበቃ ልማት ሥራዎችን ከሌሎች ልማት ሥራዎች ጐን ለጐን አጠናክሮ መቀጠል ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ዕውን ለማድረግ ወሳኝ ከመሆኑም ባሻገር የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ገጽታን ከመቀየር አኳያ የራሱ የሆነ አዎንታዊ ድርሻ ያበረክታል፡፡

የክልሉ ግብርና ከኢንዱስትሪው ጋር ተመጋቢ እንደመሆኑ መጠን ክፍለ ኢኮኖሚው ወደ ኢንዱስትሪ ልማት ለሚያደርገው ጉዞ ፈር ቀዳጅ በመሆኑ የከተማንና የገጠርን ትስስር በማጠናከርና መዋቅራዊ የሽግግር ለውጥ በማምጣት ኢኮኖሚው ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፍ በማሸጋገር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም አርሶ አደሩን (በተለይም ሴቶችን በማደራጀት በተለያዩ የገቢ ምንጮች በማሣተፍ ከግብርና ውጭ በሆኑ ሥራዎች አደራጅቶ ከአነስተኛ ይዞታ በሚገኘው ገቢ ለቤተሰቡ ፍጆታና ሌሎች ወጪዎችን እንዲሸፍን ከግብርና ውጭ በሆኑ በሌሎች ሥራዎች እንዲሠማሩ ማስቻል፣የገጠር ልማት ፈንድን በማስፋፋት ፣ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች በማስፋፋትና ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ በማድረግ ፣ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከሚታይባቸው አካባቢዎች በተጠናና በታቀደ መልኩ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሠፈራ ኘሮግራምን በማካሄድ የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ገጽታንና ባሕሪያት  በመቀየር ሂደት ጉልህ ሚና ይጫወታው፡፡ እንዲሁም በምግብ ምርት ራስን ለመቻል በሚደረገው ርብርብ በቤተሰብ ደረጃ የተለያዩ አዳዲስ የልማት ፓኬጆች ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ድህነትን ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ የተፈጥሮ አካባቢ የተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ የደን መመናመንን፣የአፈር መከላትንና በረሃማነትን በመከላከል አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስፋፋት ለገጠሩ ሕዝብ መሠረተ ልማት እንዲስፋፉ በማድረግና ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## <u>2.3.3 በግብርናውና ገጠር ልማት ሴ/ር በልማት ዕቅድ ተካተው ተግባራዊ የሚሆኑ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች</u>

- ከክልሉ ኢኮኖሚ በተለይም ከግብርናና አካባቢ ጥበቃ ልማት ጋር ያልተጣጣመውን ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሴክተሩ ልማት ላይ እያመጣ ያለውን አሳስፈላጊ ገጽታ ዙሪያ ሕብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝና ተፈላጊውን የባሕሪይ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችል ቅስቀሳና ትምህርት እስከታችኛው

የአስተዳደር እርከን ለማዳረስ በሴክተሩ የልማት ዕድቅ / ፕሮግራም በማካተት ተግባራዊ ማድረግ

- በከፍተኛ መጠን እያደገ የሚገኘው የገጠሩ ኅብረተሰብ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጠቀሜታ በሚገባ ተገንዝቦ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በቀበሌ ደረጃ ያሉትን የልማት ሠራተኞቹን በመጠቀም ለህብረተሰቡ በስፋት እንዲዳረስ ዕቅድ ነድፎ ለተግባራዊነቱም ዘርፈ ብዙ ርብርብ ማድረግ
- የአፈር መሸርሸርና ለምነትን ለመጠበቅ ዘመናዊ የአፈር ጥበቃ ዘዴዎችን መከተልና በግብርና ልማት ሠራተኞች አማካይነት የገጠሩን ኅብረተሰብ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የመኖር ሕልውናውን ለማረጋገጥ በልማት ዕቅድ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የደን ሀብት አያያዝና እንክብካቤን በሚመለከት በአሁኑ ወቅት በፍጥነት እየወደመ ያለውን ደን በመንከባከብና መልሶ በመትከል በየዓመቱ እያንዳንዱ አርሶ አደር አካባቢውን እንዲለማ አዳዲስ ፓኬጆችን በማቅረብ በልማት ዕቅድ ውስጥ አስገብቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የክልሉን የደን ሀብት ለጥፋት ከሚዳርጉት ምክንያቶች አንዱ ለማገዶና ለግንባታ ጉዳይ ማዋል ስለሆነ ለገጠሩ ኅብረተሰብ በተለይም ለሴቶች አማራጭ የኃይል ምንጮችንና የግንባታ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ያለውን ጫና ትርጉም ባለ መልኩ ለመቀነስ የተለያዩ ስልቶችን መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን ከማስፋፋት አንፃር በአሁኑ ወቅት በዝናብ ብቻ ከሚገኘው ምርት የክልሉን ህብረተሰብ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ አዳጋች ነው:: ስለሆነም በዓመት ከ2-3 ጊዜ ማምረት እንዲቻል የመስኖና ሌሎች የውሃ ምንጮችን ስቦ የገጠሩ ሕዝብ እንዲጠቀም ማስቻል፣
- የግብርና ምርትን ከአግሮ ኢንዱስትሪ ጋር ለማስተሣሰርና ለአርሶ አደሩ የተሻለ ዋጋና ገበያ ማስገኘት እንዲችሉ አግሮ ኢንዱስትሪዎችን በየገጠሩ በማቋቋም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ትስስሩን ከሥነ-ሕዝብ ገጽታዎች ጋር መቀናጀትና በልማት ዕቅድ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ወጣቶችንና ሴቶችን በማደራጀት በተለያዩ የግብርና ሥራዎች ተሣታፊ እንዲሆኑ ማድረግና በአጠቃላይ በገጠሩ የሚገኙትን የሴቶችና የወጣቶች የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት በልማት ዕቅድ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በግብርና ልማት ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎችን በመለየትና በመከለል ማልማትና በገጠር አካባቢ ኢኮኖሚ ቱሪዝምን ማስፋፋት

- ባሕላዊ አገር በቀል የአፈርና የአካባቢ ጥበቃ ልምዶች ከአካባቢያቸው ተሞክሮ በመቅሰም ወደ ሌላ አካባቢ ማስፋፋት የኅብረተሰቡን የልምድ ልውውጥ በማዳበር ተግባራዊ ማድረግ

## 2.4 ሥነ-ሕዝብና ሥርዓተ ፆታ

### 2.4.1 ሥነ ሕዝብ በሥርዐተ ፆታ ላይ ያለው ተፅዕኖ

ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ያልተመጣጠነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መኖር በቂ መሠረተ ልማት አቅርቦት እንዳይኖር ተጽዕኖ ያደርጋርል። ይህም የሚሆነው ያለው የመሠረተ ልማት ግንባታ ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር እኩል ለእኩል መሄድ ስለማይችል ነው። የትምህርት ሴክተር በተለየ መልኩ የሰዎችን አስተሳሰብ በመለወጥ ከፍተኛውን ሚና መጫወት ሲችል ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ባለበት ሁኔታ ግን አገልግሎትን ለማዳረስ አዳጋች ይሆናል። ይህ የትምህርት ማነስም ኀብረተሰቡ የህዝቡ ግማሽ ክፍል ለሆኑት ሴቶች የተዛባ አመለካከት እንዲኖረው ተጽእኖ ያደርጋል። ይህ ተጽእኖም እየጐለበተ መጥቶ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኀበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የበኩላቸውን እንዳይወጡ በማድረግ ተሣትፏቸውን አናሳ ያደርገዋል።

የክልሉ የ2000 ዓ.ም መረጃ እንደሚያመለክተው በትምህርት በኩል ያለውን ሁኔታ ስናይ በመዋዕለ ህፃናት ከተመዘገቡ ህፃናት ውስጥ 52% ወንዶች ሲሆኑ 48% ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው። ይህ የሴቶች የትምህርት ተሣትፎ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ በተለይም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በእጅጉ የተመናመነ ነው። በጤናም በኩል ሲታይ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ሴቶች ከአራት እጥፍ በላይ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ/ የመያዝ እድላቸው ሠፊ ሆኖ እና የማርገዝና የመውለድ የተፈጥሮ ህግ እያለባቸው በጤና አገልግሎት ግን ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ አልሆኑም። በሌሎች የፖለቲካና መሠል ተሣትፎዎችም እኩል ተጠቃሚ አልሆኑም ። ይህም በወንዶችና ሴቶች መካከል ያለውን ቅርርብ በማጥበብ የፆታ እኩልነትን በማሳነስ ወንዶችን የበላይ ሴቶችን ግን የበታች ያደርጋል። ይህም ከክልሉ ህዝብ መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑትን ሴቶች የውሣኔ አቅም በማሳጣት የሥነ-ሕዝብ ችግርን ጭራሽ እንዲባባስ ያደርጋል።

### 2.4.2 *ሥርዐተ ፆታ በሥነ-ሕዝብ ላይ ያለው ተፅዕኖ*

*ሥርዐተ ፆታ በሥነ-ሕዝብ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመናገር በመጀመሪያ በክልላችን ያለውን የሥርዓተ ፆታ ሁኔታ መገምገም ተገቢ ነው፡፡ በክልሉ ያለው የፆታ ሥርዓት ሲታይ እንደሀገሪቱ ሁሉ በወንዶች የበላይነትና ውሣኔ ሰጭነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሴቶች ግን ከውሣኔ ሰጭነቱ በእጅጉ ርቀው ይገኛሉ፡፡ የክልሉ መንግሥት ይህን ሁኔታ ለማጥበብ በሴቶች ጉዳይ ቢሮ በኩል ብዙ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም ያለውን የፆታ እኩልነት ያለመኖር ችግር ሥናይ ብዙ መሰራት እንደሚጠበቅ አመልካች ነው፡፡*

*ሥርዓተ ፆታ በሥነ-ሕዝብ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ምንድነው? የሚለውን ስናይ*

- ሴቶች ተገቢውን የጤና እንክብካቤ ባለማግኘታቸው የእናቶችና ህፃናት ሞት በክልሉ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡
- ሴቶችን በማስተማር ቤተሰብን ብሎም ሀገርን በፍጥነት መለወጥ የሚቻልበትን የልማት ጉዞ ሴቶች ትምህርት ባለማግኘታቸው ምክንያት የልማት ፍጥነት እንዲገታ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡
- የክልሉን የውልደት መጠን ከፍተኛ እንዲሆን የራሱን አስተዋጾኦ ያበረክታል፡፡ ይህም የህዝብ ቁጥር ዕድገት እንዲፋጠን አድርጓል፣
- ሴቶች ለኤች.አይ.ቪና ሌሎች ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲጋለጡ ያደርጋል፣
- በምርታማነትና ምርትን በማሣደግ ከፍተኛውን ሚና መጫወት የሚችሉትን ግማሽ ያህሉን የኀብረተሰብ አካል ከተሣትፎ ይገታል፣
- ሴቶች ከልማት ይልቅ ጊዜአቸውን ልጅ በማሣደግና በሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ብቻ በመወሰን ህይወታቸውን እንዲገፉ ያደርጋል፣

### 2.4.3 *በሥርዐተ- ፆታ ዙሪያ በሚቀረፁ ኘሮግራሞችና ዕቅዶች ውስጥ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች*

*ሥርዓተ ፆታን በልማት ዕቅዶቻችን ውስጥ ከማስገባታችን በፊት በመጀመሪያ ሥነ-ሕዝብና ሥርዓተ ፆታ ያላቸውን ትስስር በደንብ ለይቶ መረዳትና ዕቅዱን ለማቀድ የሚያስፈልጉ ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብና መተንተን አስፈላጊ ነው፡፡*

እነዚህ *መረጃዎችም*

- በክልሉ ያለው አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር በፆታ፣ በእድሜ

- ከአጠቃላይ የመንግሥትና የግል ተቀጣሪዎች ውስጥ የሴቶችን ድርሻ በመቶኛ ለይቶ ማወቅ ፣
- ሴቶች በመዋዕለ ሕፃናት፣ በአንደኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያላቸውን የተሣትፎ መጠን ማወቅ
- የሴቶችን የትምህርት መጠነ መቋረጥ በየትምህርት ደረጃው ለይቶ ማውጣት
- እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ሴቶች በትምህርት፣በጤናና በሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ተሣትፎዎች ያላቸውን ሚና የሚያሳድጉ እቅዶች በሥርዐተ ፆታ ዙሪያ በሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ መካተት አለባቸው፡፡

- በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ የኀብረተሰቡን አስተሳሰብ የሚያስተከክሉ ውይይቶች እንዲካሄድ ማድረግ፣
- በሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ላይ ወንዶችን ከሴቶች እኩል የራሳቸውን ተሣትፎ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸውን ስልጠና መስጠት፣
- ሴቶች በኢኮኖሚ በኩል ከጉለበቱ የውሣኔ ሰጭነት ሚናቸው በእጅጉ ስለማጠናከር የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚያጉለብቱ ስትራቴጂዎችን መንደፍ
- የሴቶችን የትምህርት ተሣትፎ ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ የድጋፍና የክትትል እርምጃዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣
- የሴቶችን የህመምና ሞት መጠን የሚቀንሱ የጤና መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት መጣር ፣
- ሴቶችን የሚያበረታቱ የሥራ እድሎችን መፍጠር፣
- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማኀበረሰቡ በራሱ ተወያዖቶ በሚያስወግድበት የማኀበረሰብ ውይይቶች በሌሎችም ማኀበራዊ ጉዳዮች ወቅት ሴቶች ጠንካራ ተሣትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል፣
- የሴቶችን መብት በሚያስጠብቁ ሕጎችና ደንቦች ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሥራት
- ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ሴት ህፃናት በራሳቸው መተማመን የሚያስችላቸውን ሥልጠናን ድጋፍ እንዲያገኙ ማስቻል፣
- የሴቶችን የትምህርት መጠን መቋረጥ ለመግታት የሚያስችሉ ማኀበራዊ ህጐችን በኀብረተሰቡ እንዲወሰኑ በማስቻል ተግባራዊነታቸውን መከታተል፣

## 2.5 ሥነ-ሕዝብና ወጣቶች

### 2.5.1 ሥነ-ሕዝብ በወጣቶች ላይ ያለው ተፅዕኖ

በፍጥነት እያደገ የሚመጣ የሕዝብ ቁጥር እድገት የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስ በሚደረግ ርብርብ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ አለው። ይህም በየትኛውም እድሜ ደረጃ የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚመለከት ሲሆን በተለይ ወጣቶችን ከሌሎች ጐላ ባለ ሁኔታ ይነካል።

እንደ ዓለም አቀፍ ጤና ድርጅት መረጃ ወጣት ማለት ዕድሜው ከ10-24 ዓመት ያሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትት ቢሆንም ብዙ ሀገራት ወጣት ለሚለው ትርጉም ከኢኮኖሚያዊ የአኗኗርና ባህላዊ እሴቶቻቸው አንፃር የተለያየ የዕድሜ ደረጃን ይጠቁማሉ። በ1996 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊስ ሰነድ እንደሚያሳየን ወጣት ማለት ዕድሜአቸው ከ15-29 ዓመት ያሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያካትት ሲሆን የአጠቃላዩን ሕዝብ አንድ ሶስተኛ እንደሚሆን ይገመታል።

የክልላችን ወጣቶች እንደሌላው የኅብረተሰብ ክፍሎች አስከፊና እጅግ ውስብስብ ለሆኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ናቸው። በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የሀገራችንም ሆነ የክልላችን ወጣቶች በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይገኛሉ።

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በወጣቶች ላይ ያለው ተፅዕኖ

- ከፍተኛ የውልደት መጠን ሲኖር የእድሜ ስብጥሩ በፈጠነ መልኩ በወጣት ሀይል ይሞላል በመከተልም የውልደት መጠኑ እንዲያድግ ያደርገዋል።
- ወጣት ተኮር የሆኑ የጤና፣ የትምህርትና የሌሎች አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት አስቸጋሪ ይሆናል።
- ሥራ አጥነት፣ሴተኛ አዳሪነት፣ያልተፈለገ እርግዝና፣ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ሕገ ወጥ ውርጃና ሌሎች ማኅበራዊ ችግሮች ይባባሳሉ።
- ወጣቱ ትውልድ ለክልሉም ሆነ ለሀገሪቱ ማድረግ የሚኖርበትን ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎዎች በመረጃና ትምህርት እጦት ምክንያት ሳያደርግ ይቀራል።
- በአካባቢው ያለውን ድህነትና ችግር ለመሸሽ ሲል ወጣቱ ቀየውን ትቶ ይሠደዳል በአጠቃላይ ወጣቶች ማግኘት የነበረባቸውን ማንኛውንም አገልግሎት በከፍተኛ ቁጥር በሚያድግ የህዝብ ብዛት ምክንያት በሚመጣ ጫና ሳያገኙ ይቀራሉ።

ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊ ተልዕኮ እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ ለውስብስብ ማኀበራዊ ችግሮች ያጋልጣቸዋል፡፡

በመሆኑም በማናቸውም የወጣቶችን ችግሮች የሚፈቱ እቅዶችና ኘሮግራሞች ላይ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ማካተት ይገባል፡፡ ይህን ለማሳካት የሚያስችሉ ወጣቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችም አብረው መሰብሰብና መተንተን አለባቸው ምክንያቱም እንደሀገራችን የእድሜ አወቃቀር ከአጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ይዞ የሚገኘው ወጣቱ በመሆኑ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ምክንያት በሚከሰቱት የድህነትና የኃላ ቀርነት ተፅዕኖዎች ሥር ከሚወድቁ የኀብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ወጣቶች ሰፊ ድርሻ እንዲይዙ ያደርጋቸዋል፡

### 2.5.2 <u>ወጣቶች በሥነ-ሕዝብ ላይ የሚኖራቸው ተጽእኖ</u>

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከክልሉ አጠቃላይ ሕዝብ የወጣት ቁጥር ከ30 በመቶ በላይ ነው፡፡ እነዚህ ከክልሉ ሕዝብ ቁጥር አብዛኛውን የሚሸፍኑት ወጣቶች ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ማኀበራዊ፣ባህላዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው፡፡ የወጣቱ ክፍል በአመዛኙ ያጋጠሙት ማኀበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊያዊ ችግሮች መካከል ለአብነት የሚጠቀሱት ሥራ አጥነት፣ በአደንዛዥ ዕጾችና አልኮል (ጫት ፣ ሲጋራና ሀሺሽ) ሱሰኝነት፣የመዝናኛና የወጣት ማዕከላት እጥረት ፣ጥንቃቄ በጎደለውና ያለዕድሜ በሚጀመር ልቅ የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ምክንያት የሚከሰቱት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ያልተፈለገ እርግዝና ፣ውርጃ ፣በአጋጣሚ በሚፈጠርና የለበቂ አቅም የቤተሰብ ኃላፊ መሆን ፣ጉዳና ተዳዳሪነት ፣የቤተሰብ ጥገኛ መሆን ወዘተ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው፡፡

ከፍ ብለው የተጠቀሱትን የወጣቱን ማኀበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊያዊ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ መንግሥት ፖሊሲን በማውጣትና ለፖሊሲው አፈጻጸም ምቹ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ የወጣቱን ዘርፈ-ብዙ ችግሮችን በሂደት ለመቅረፍ እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባራት መካከል በጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ፓኬጅ ወጣቱ በብቃት እንዲሣተፍ ማድረግ፣ ለወጣት የመዝናኛና የተለያዩ አገልግሎት የሚሠጡ ማዕከላትን መገንባት፣ወጣት ማኀበራትን ማደራጀትና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ የወጣቱን ሚና ማጎልበት ፣ወጣቶች በሥነ-ሕዝብና ተያያዥነት ባላቸው በሥነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሥነ-ሕዝብና የቤተሰብ ኑሮ ትምህርት (Population and Family Life Education) በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች በመደበኛ ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲማሩ መደረጉ ለአብነት ይጠቀሣሉ፡፡ ከዚህ

ጥረት ጎን ለጎን ወጣቶች በሥነ-ተዋልዶ ጤናና በሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ፣እንዲመካከሩና እርስ በርሳቸው እንደሚማሩ ለማስቻል በክልሉ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ክበባት ተቋቁመው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

የክልሉን አላስፈላጊ ሥነ-ሕዝብ ገጽታን ባህሪያት በመቀያየር ረገድ ወጣቱ የኀብረተሰብ ክፍል አዎንታዊና አሉታዊ ድርሻ እንደሚያበረክት ዕውን ነው፡፡
ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የወጣቱን ሁለንተናዊ ገጽታን ለመለወጥና የኑሮ ሁኔታዉን ለማሻሻል በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው፡፡ የወጣቱን ክፍል በተለያዩ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዘርፎች ማሣተፍና በሥነ-ሕዝብና ልማት ርዕሠ- ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ሥልጠናዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን ወጣቱ አዎንታዊ ለውጥ በማምጣት ከፍተኛ የሆነው የወጣቱን ቁጥር ለማርገብና የሚፈለገውን ዲሞግራፊያዊና ኢኮኖሚያዊ ሽግግር ማድረግ ይቻላል፡፡

በሌላ አንፃር ደግሞ ወጣቱ የኀብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ ቁጥር የያዘ በመሆኑ ከፍተኛ የውልደት መጠን እንዲኖር በማድረግ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እንዲኖር ምክንያት ይሆናሉ፡፡

በክልላችን ከ0-14 ዓመት የእድሜ ክልል የሚገኙት ህፃናት በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሲሆን ከ15-64 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው አምራች የኀብረተሰብ ክፍል ቁጥር ከመጀመሪያው የሚቀንስበት እና ከ65 እድሜ በላይ የሚገኙት አረጋውያን ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ይህም የሶስት ማዕዘን ቅርጽ ያለው (population payramid) ይህ ትክክለኛ ያልሆነ ቅርጽ እንዲኖር ከሚያደርጉት ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ በየአመቱ ከታዳጊነት ወደ ወጣትነት የሚሸጋገሩበት ቁጥራቸው ከፍተኛ መሆንና በወጣትነት የሚገኙት ቁጥራቸው ከፍተኛ በመሆኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕፃናትን ይወልዳሉ፡፡ በተለይም ሴቶች ቶሎ የማግባት ዕድላቸው ሰፊ በመሆኑና ብዙ ልጆችን ስለሚወልዱ የዕድሜ ስብጥርና አወቃቀር በማዛባት በኩል አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም ወጣቱ ክፍል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ህፃናት በመውለድ የእድሜ ስብጥርን ያዛባል፡፡
በታዳጊ አገሮች የሚገኙት ወጣቶች በአብዛኛው ለስነ-ሕዝብ ችግሮች የተጋለጡ በመሆኑ ፈጣን የውልደት መጠን እንዲኖር አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በቤተሰብ ደረጃ በሚኖረው

ፈጣን ውልደት ምክንያት በእያንዳንዱ አባወራ ቤት በርካታ ልጆች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በቤተሰብ ደረጃ ጥገኝነት በስፋት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

### 2.5.3 በወጣቶችና ስፖርት ሴክተር የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካትተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች

በወጣቶችና ስፖርት ሴክተር ሊካተቱ ከሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ

- ከኢኮኖሚው የቀደመ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የተነሣ የሚከሰተው ሥራ አጥነትን መቅረፍ
- ወጣት ተኮር የሆነ የተዋልዶ ጤና አገልግሎትና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት (Youth friendly RH/ FP Services) እንዲያገኙ ማድረግ
- ወጣቶች በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት የማግኘት ጠቀሜታና በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥና የባሕርይ ለውጥ የማምጣት ሥራ መሥራት
- ወጣቶች አልባሌ ሥፍራ እንዳይውሉ የወጣቶች መዝናኛ ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር፣
- የሀይማኖት ተቋማትንና የሲቪክ ማህበራትን በመጠቀም ወጣት ተኮር የተዋልዶ ጤና አገልግሎትን በስፋት መስጠት ከሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ አንፃር ይጣራል፡፡
- ኘሮግራሙ /ዕቅዱ የሚያተኩረው ሥራ- አጥ ወጣቶችን ሥራ ለማስያዝ ከሆነ፣ዕቅዱ ለሚያቅፈው ቦታና ጊዜ በተመለከተ የሥራ አጥነት መጠንን (Employment rate) መሠረት በማድረግ ብዛቱን ማስላትና በዕቅዱ ውስጥ ማካተት ተገቢ ይሆናል፡፡

እነዚህ መረጃዎች ባብዛኛው የሚገኙት በፋ/ኢ/ል/ቢሮ መረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት፣የሥራ ሂደት ከሕዝብ ቆጠራ ውጤት (ስታቲስትክስ ባለሥልጣን)፣ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ኤጄንሲ ወይንም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መያዶች ሊሆን ይችላል፡፡ ዕቅዱ በዞን፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚታቀድ ከሆነና በቀጥታ ለሥፍራው የሚሆን ጥናታዊ መረጃ ከሌለ የክልሉን ወይም የዞኑን መረጃ ወስዶ ለዚያ አካባቢ (ቦታ) በሚሆን መልኩ ሳይንሣዊ ስሌት (ግምት) ማድረግ የተሻለ ይሆናል፡፡

- የዕቅዱ/ የኘሮግራሙ ዓላማ ወጣት ተኮር የሆነ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት Youth friendly RH/ Services) ለመስጠት ወይም የወጣት ማዕከላትን Youth Centers) ለማቋቋም ወይም በተዋልዶ ጤና ግንዛቤ ለመስጠት ከሆነ ደግሞ ከአጠቃላይ ሕዝብ ውስጥ ከ15-29 ዕድሜ ውስጥ ያሉትን ለይቶ አውጥቶ ብዛቱን ማወቅና በየአመቱ ምን ያህል ለውጥ እንደሚያመጣ የሕዝቡን ቁጥር ዕድገት መጠን (Population

Groth Rate) መሠረት በማድረግ አስልቶ መጠቀም ነው። ለዚህ ስሌት መሠረት የሚሆነውን መረጃ ከሕዝብ ቆጠራ ውጤት ላይ ማግኘት የሚቻል ሲሆን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጠንንም ጨምሮ ከኢትዮጵያ ስታቲስትክስ ባለሥልጣንም ሆነ በየደረጃው ከፋ/ኢ/ል/መ/ቤቶች ሥር ከሚገኙት ከሥነ-ሕዝብ ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት እንዲሁም ደግሞ ከመረጃ መሰብሰብና ማሠራጨት ዋና የሥራ ሂደት ማግኘት ይቻላል።

## 2.6 ሥነ-ሕዝብና ማኅበራዊ ችግሮች

### 2.6.1 ሥነ-ሕዝብ በማኅበራዊ ችግሮች ላይ ያለው ተጽእኖ

#### 2.6.1.1 ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሥራ አጥነት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሚታይበት ኅብረተሰብ ዘንድ ወጣት የሆነ ሕዝብ የሚበዛበት ከመሆኑም በላይ በመስሪያ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ሕዝብ በጣም በርካታ ይሆናል። ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጥገኝነት እንዲበዛና የዕለት ፍጆታ በዘቶ ቁጠባ እንዲቀጭጭ በማድረግ ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ ስለሚያደርግ ፣የሥራ ዕድሎችን የሚፈጥሩ ኢንቨስትመንቶች ውስን ስለሚሆኑ በጣም በርካታ የሆነውን የሠራተኛ ሃይል ማስተናገድ ስለማይችሉ ሥራ አጥነት እንዲስፋፋ ያደርጋል።

#### 2.6.1.2. ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ተዳዳሪዎች በወላጅ አልባ ሕፃናት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ

እያንዳንዱ ቤተሰብ መጥኖ ቢወልድ ፣ወላጅ በሚገባ ማሣደግ የሚችል ልጅ ብቻ ስለሚወልድ ከአቅም በላይ ሆነው ወደ ጐዳና የሚወጡ ልጆችና አሣዳጊ አልባ ሕፃናት ቁጥር እጅጉን ይቀንሳሉ።

ልማት በጣም ካደገ ኀብረተሰቡና መንግሥት ራሱ ለጐዳና ተዳዳሪዎችና ለወላጅ አልባ ሕፃናት የመማሪያና የመደገፊያ ተቋማትን በነፃ ስለሚያቀርብላቸው የመማርና ራስን የማሻሻል ዕድሎችን ማግኘት ይችላሉ። የኢኮኖሚ ልማት አነስተኛ በሆነበት ማኅበረሰብ ግን ጐዳና ተዳዳሪነትና ሌሎች ማኅበራዊ ጠንቆችም እየጨመሩና እየተባባሱ ይሄዳሉ።

#### 2.6.1.3. ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ደጋፊ በሌላቸው አረጋዊያን ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖ

ከኢኮኖሚ አቅም ጋር የተወለዱ ብዙ ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ ያለ አባወራ እነዚህኑን ልጆች የዕለት ጉርስ ለመሸፈን ጥረት ከማድረግ በስተቀር ያለውን ገቢ ቆጥቦ ማስቀመጥ

ስለማይችል በእርጅና ጊዜው ያለምንም ጥራት ባዶ እጁን ለመቅረት ይገደዳል፤ እነዚያ ያለበቂ ትምህርትና መረታዊ ፍላጐቶቻቸው ሣይሟሉላቸው የሚያድጉት ልጆች ራሳቸውን ካለመቻላቸውም በላይ ወላጆቻቸውን ለመደገፍ የማይችሉ ይሆናሉ። አባትም ያለጥሪትና ያለደጋፊ ስለሚቀሩ በሽምግልና ወቅት ረዳት አልባ የመሆን ዕድል ሊገጥማቸው ይችላል።

### 2.6.1.4. ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት በሴተኛ አዳሪነት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ

ከኢኮኖሚ አቅም ጋር የማይጣጣም ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ሴቶች እንዳይማሩ ሥራ እንዳያገኙ ስለሚያደርጋቸው እንዲሁም ደግሞ አንዳንዴ ሊባል አስከፊ ተፅዕኖ ስለሚያጋልጣቸው የእለት መተዳደሪያ ለማግኘት ያለፍላጎታቸው ሴተኛ አዳሪነትን እንደገቢ ማስገኛ አድርገው ይሰማሩበታል። ይህም ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ለመሳሰሉት ገዳይና አሰቃይ በሽታዎች የሚያጋልጣቸው ጊዜ ይበልጣል።

### 2.6.1.5. ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ጥፋተኝነት ላይ ያለው ተፅዕኖ

ከኢኮኖሚ ጋር ያልተመጣጠነ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ኢኮኖሚው ሊሸከመው የማይችለውን እጅግ በርካታ ለሥራ የደረሰ ግን ያልተማረ ወይም ጥቂት ብቻ የተማረ ወጣት እንዲኖር ያደርጋል፤ ኢኮኖሚው ለእያንዳንዱ ወጣት የሚሆን የሥራ ዕድል መፍጠር የማይችል በመሆኑ ሥራ አጥነት ይበዛል፤ ይህም እየበዛ ሲሄድ ወጣቱ በአምራችነት ፋንታ ማኅበራዊ ሰላምን የሚያናጋ ወጣት ጥፋተኛ እየበዛ እንዲሄድ ያደርጋል። በሌላ በኩል ደግሞ መጥኖ ካለመውለድ የተነሣ ለመማር ያልቻሉትና በሥርዓት ታንፀው የማደግ ዕድል ያላገኙት ጐዳና ተዳዳሪ ሕፃናት ሲያድጉ ወጣት ጥፋተኛ የመሆን ዕድላቸው ሠፊ ነው።

## 2.6.2 ማኅበራዊ ችግሮች በሥነ-ሕዝብና ልማት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ

### 2.6.2.1. ሥራ አጥነት በሥነ-ሕዝብና ልማት ላይ ያለው ተፅዕኖ

ሥራ አጥ የሆኑ ሰዎች እየበዙ በሄዱ ቁጥር አምራች በሆነው የኅብረተሰቡ ክፍል ላይ የጥገኝነት ጫና እየጨመረ የሚመጣ ሲሆን ይህም በበኩሉ አምራች ወገኖች ያገኙትን ገቢ በዕለት ፍጆታ ላይ ብቻ እንዲያሚጥጡ በማድረግ ቁጠባን በማመናመን ኢንቨስትመንት እንዲዳከም ያደርጋል። ኢንቨስትመንት ሲዳከም ልማት እንዳይፋጠን በማድረግና ሠራተኛ የሰው ኃይል የሚቀጠርበትን ዕድል በማጥበብ መልሶ ሥራ አጥነት ይባስ እንዲጨምር ያደርጋል።

በሌላ በኩል ስናየው ደግሞ ሥራ አጦች እየበዙ በሄዱ ቁጥር ለእለት ጉርሳቸው ሲሉ የአምራቹን ክፍል ምርትና ንብረት ወደ መስረቅ/መዝረፍ፣ደን ጨፍጭፈው የሚሸጡና ሌሎች ህገወጥ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ወጣት ጥፋተኞች ይበዛሉ ፣ሰላምና መረጋጋት ስለሚጠፋም ኢንቨስትመንት እንዲቀንስና አምራቾች በጥቃት ሥር ስለሚወድቁ ምርት ሊቀንስና ሰላማዊ ሰዎች የመሥራትና የመኖር ዋስትና ሊያጡ ይችላሉ። በዚህም ልማት እንዳይጠፋን የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጠራል፤ይህም መልሶ ድህነትንና ሥራ አጥነትን ያባብሳል፣ልማትን ወደ ኋላ ይጐትታል።

### 2.6.2.2 ጐዳና ተዳዳሪነትና ወላጅ አልባ ሕፃናት በሥነ-ሕዝብና ልማት ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖ

ጐዳና ተዳዳሪና ወላጅ አልባ ሕፃናት የሚያስተምራቸው፣ የሚመግባቸውና ጥሩ ሥነ-ምግባር ይዘው እንዲያድጉ የሚንከባከባቸው አካል ስለሌለ ከነዚህ ሕፃናት መካከል ለወደፊቱ ሀገርን የሚገነባ፣ ሀላፊነት የሚሰማው ፣ክህሎት የጨበጠና በሥነ-ምግባር የታነፀ ዜጋ ማግኘት አስቸጋሪ ሲሆን  በአንፃሩ ደግሞ ባብዛኛው ሥርዓተ አልበኛነት ፣ወጣት ጥፋተኛነት የሚበዛበት ፣ለማኅበረሰቡ ፀጥታ ጠንቅ የሆነና አሉታዊ ጐን የሚበዛበት ትውልድ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ በዚህ የተነሣ ልማትን የሚያፋጥንና ማኅበረሰቡን የሚገነባ ሳይሆን በአንፃሩ ልማትን ወደኋላ የሚጐትትና አፍራሽ ዜጋ እንዲበዛ ምክንያት ይሆናል።

ይህም መልሶ ጐዳና ተዳዳሪነትና ወላጅ/አሳሣዳጊ/ አልባ ሕፃናት እንዲበዙ ያደርጋል። እነዚህ ልጆች ሲያድጉና ሲያገቡም የተማሩ ባለመሆናቸው ቤተሰብ ምጣኔ የማይጠቀሙና ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እንዲኖር የሚያበረታቱ ናቸው።

### 2.6.2.3 ሴተኛ አዳሪነት በሥነ-ሕዝብና ልማት ላይ ያለው ተፅዕኖ

ሴተኛ አዳሪነት በልማት ላይ ለመሣተፍ የሚችሉ ሴቶችን አፍራሽ ሚና ባለው ሥራ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ልማትንና ጤንነትን ይጐዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ሴተኛ አዳሪ ሴቶች ለሀገሪቱ ልማት ላይ በጐ አስተዋጽኦ ያላቸው አምራችና የተማረ የሰው ኃይል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመሳሰሉ ጐጂና ገዳይ በሽታዎች እንዲጋለጡ ምክንያት በመሆን ልማትን እጅግ ይጐዳሉ፤ብዙ ወላጆችና አምራቾች በኤድስ የተነሣ ሲሞቱ ብዙ ወላጅ አልባና አሳዳጊ አልባ ሕፃናት ይፈጠራሉ። ይህም ደግሞ ሌላው የሥነ-ሕዝብ ችግር ነው።

### 2.6.2.4 ወጣት ጥፋተኛነት በሥነ-ሕዝብና ልማት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ

ወጣት ጥፋተኛነት በልማት ዕድገትና በማኀበራዊ ፀጥታ ላይ አፍራሽ ሚና አለው፡፡ ፀጥታና መረጋጋት በጐደለበት ቦታ ሁሉ የኗሪው ኑሮ ከመደፍረሱ በተጨማሪ ኢንቨስተሮች ዋስትና የማጣት ስሜት ስለሚሰማቸውና ኢንቨስት ለማድረግ ስለማይበረታቱ የልማት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ወጣት ጥፋተኞች የለማውን ልማት በቀጥታ የሚያጠቁና የሚያበላሹ በመሆናቸው የኢኮኖሚ ዕድገትና የሰላማዊ ኑሮ "ነቀዞች" ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.6.3 በማኀበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሚቀረጹ ዕቅዶችና ኘሮግራሞች ውስጥ ተካተው ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች

- ዕቅዱ ወይም ኘሮግራሙ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ የሚሠራ ከሆነ ዕቅዱ የሚከናወንበትን ቦታ በሚመለከት የቦታው ሥራ አጥነት መጠን ላይ በመንተራስ በዚያ በዕቅድ ዓመት (ወቅት) የሥራ አጦች ብዛት ስንት እንደሆኑ በመለየትና በዕቅዱ ውስጥ ማካተት ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ የሥራ አጥነትን የሚያሳይ መረጃ ለዚያ ቦታ ከሌለ ሥፍራው የሚገኝበትን ከተማ አስተዳደር፣ ወረዳ፣ ዞን ወይም ክልል የሥራ አጥነትን መጠን መረጃ በመጠቀም ማስላት ይቻላል፡፡
- ኘሮግራሙ ወይም ዕቅዱ በጐዳና ተዳዳሪነት ላይ የሚሠራ ከሆነ ዕቅዱ የሚተገበርበትን ከተማ (ሥፍራ) በሚመለከት የጐዳና ተዳዳሪዎቹን ብዛት በዚያ ዕቅድ ወቅት ስንት እንደሚሆኑ በማስላት ወይም ሳይንሣዊ ግምት በመውሰድ በዕቅዱ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ዕቅዱ ወይም ኘሮግራሙ ለብዙ ዓመታት የሚያገለግል ከሆነ በየዓመቱ ያለውን የቁጥር ለውጥ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡
- የዕቅዱ ወይም የኘሮግራሙ ትኩረት ወላጅና (አሣዳጊ) የሌላቸው ሕፃናትን የሚመለከት ከሆነ ዕቅዱ የሚተገበርበትን አካባቢ (ሥፍራ) በሚመለከት በዚያ ዕቅድ ዓመት (ዓመታት) ወላጅ (አሣዳጊ) አልባ ሕፃናት ስንት እንደሆኑ በመለየት ማስላት ወይም ሳይንሣዊ ግምት በመውሰድ በዕቅዱ ውስጥ አካትቶ መስራት የሚገባ ሲሆን በየአመታቱ መካከል ያለውን የቁጥር ልዩነትንም ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሊታቀድ ይገባል፡፡ ለዚያ አካባቢ የሚሆን የተጠና ጥናት ከሌላ ፣ሠራተኛና ማኀበራዊ ኤጀንሲና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የማኀበረሰብ ተቋማትና መያዶች ለሣይንሳዊ ግመታ የሚረዱ መረጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
- ደጋፊና ጧሪ የሌላቸው አረጋውያን የዕቅዱ ወይም የኘሮግራሙ ትኩረት ከሆኑ ዕቅዱ የሚተገበርበትን ቦታ (አካባቢ) በሚመለከት በዕቅድ ዓመቱ (አመታቱ) ውስጥ ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን ቁጥር ስንት እንደሚሆኑ በማስላትና በየጊዜው ያለውን የብዛት

ለውጥ ባገናዘበ ሁኔታ አካትቶ ማቀድ አስፈላጊ ነው፡፡ ለቦታው በርዕሱ የተጠኑ ጥናቶች ከሌሉ ለሣይንሣዊ ግምት የሚረዱ መረጃዎች ከሠራተኛና ማኅበራዊ ኤጀንሲና በጉዳዩ ላይ ከሚሠሩ ማኅበራትና መያዶች ሊገኙ ይችላሉ ፡፡

- ዕቅድ ወይም ኘሮግራሙ በሴተኛ አዳሪነት ላይ የሚሠራ ከሆነ በዚያ ከተማ / ክፍለ ከተማ በዕቅድ ዓመቱ (አመታቱ) የሴተኛ አዳሪዎች ቁጥር ምን ያህል እንደሚሆን በማስላት ወይም ሣይንሣዊ ግምት በመውሰድ በየጊዜው ያለውን የቁጥር ለውጥ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አካትቶ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ በክልል ወይም በዞን ደረጃ የሴተኛ አዳሪዎችን ብዛት የሚመለከት የተጠና ጥናት ከሌለ በሠራተኛና ማኅበራዊ ኤጀንሲና በሴቶች ጉዳይ መ/ቤቶች አቅጣጫን የሚያሣዩ መረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡
- ወጣት ጥፋተኛነት የዕቅዱ ወይም የኘሮግራሙ ትኩረት ከሆነ ደግሞ ዕቅዱ የሚተገበርበትን ሥፍራ (አካባቢ)ና ጊዜ በሚመለከት የወጣት ጥፋተኞች ቁጥር በየጊዜው (በየዓመታቱ) ስንት እንደሆነ በማስላት በዕቅዱ /በኘሮግራሙ ውስጥ ማካተት ይገባል፡፡ ለቦታው ወጣት ጥፋተኛነትን መጠን የሚያሣይ ጥናት ከሌለ ከዚያ አካባቢ የፖሊሲ መ/ቤት ወይም ማረሚያ ቤት አቅጣጫን የሚያሣይ መረጃ ማግኘትና ሣይንሳዊ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የኘሮግራሙ ወይም የዕቅዱ ሥፍራ (ቦታ) የሚገኝበት ዞን ወይም ክልል ያለውን መረጃ በመውሰድ ለዚያ አካባቢ በሚሆን መልኩ ማስላት ይቻላል፡፡

## ክፍል ሦስት

### የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

አንድ የልማት ኘሮግራም ወይም ኘሮጀክቱ የታለመለትን ዓላማ መምታት መቻሉንና በኘሮግራሙ ወይም በኘሮጀክቱ የታቀዱትን ግቦችንና ዝርዝር ተግባራት ያሉበትን ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው በጠንካራ የክትትል፣የግምገማና ግበረ-መልስ ሥርዓት ሲታገዝ ብቻ ነው። በመሆኑም በኘሮግራሙ ወይም ኘሮጀክቶች ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ በታቀዱት ግቦችና ዝርዝር ተግባራት ትግበራ ሂደት ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማዘርጋት በአፈጻጸም ረገድ የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየትና ተገቢ የሆኑ የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ ኘሮግራሙን ስኬታማ በማድረግ በኩል ገንቢ ሚና ይጫወታል።

ክትትል ግምገማ ዘርዝር ባለ መልኩ ስታይ ደግሞ ኘሮግራሞች በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት እየተተገበሩ ስለመሆናቸው፣ የታቀዱ የሥራ ተግበራት ወደታለሙ ውጤቶችና ግቦች እየመሩ ስለመሆናቸው በክንውን ወቅት እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች በጥልቀት ለመረዳትና እንዲሁም ላጋጠሙ ችግሮች በጥልቀት ለመረዳትና እንዲሁም ላጋጠሙ ችግሮች ዘላቂ የማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችልና ማረጋገጫ የሚገኝበት የአሠራር ስልት ነው። በመሆኑም ክትትልና ግምገማ አንድ የሥራ ተቋም ወይም ሴክተር መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል ካከናወናቸውና አሁንም በማከናወን ላይ ካለው የሥራ ተግባራት ጠቃሚ ተሞክሮዎችን በመውሰድ ወደፊት ሊሰሩ በሚታቀዱ የሥራ ተግባራት ላይ ተገቢ የሆነ ማስተካከያዎችን ለመውሰድ ይረዳል።

ክትትልና ግምገማ በሁለት በተለያዩ ግን በቅርበት በተያያዙ የሥራ ደረጃዎችና የጊዜ ሠሌዳ ሊካሄድ ይችላል። የመጀመሪያ ደረጃ የሚያተኩረው በአንድ ኘሮግራም ወይም ኘሮጀክት ውስጥ ግብዓቶችን በመጠቀም የሚገኘው ምርት ወይም አገልግሎት ሲሆን ሁለተኛው ደረጃ የሚያተኩረው ደግሞ አንድ ኘሮግራም ወይም ኘሮግጀክት ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ልማቱ ያመጣው ለውጥ ነው።

## 3.1 የክትትል መነሻ ሀሣብና መርሆና ፋይዳው

የአንድን ኘሮግራም ወይም ኘሮጀክት የሥራ ተግባራትን በጥልቀትና በስፋት ለመከታተልና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል መጀመሪያውን መደረግ ያለባቸው ቅድሚያ ሁኔታዎችን በደንብ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም የክትትል ሥርዓት በጠንካራ መሠረት ላይ የቅድሚያ ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ የመጣር

- የመንግሥትን የልማት ፖሊሲዎችን በደንብ መረዳት፣
- ዓላማና ግብ በደንብ መንደፍ
- ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት ምቹ ሁኔታዎችን መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- ትኩረት በሚሹ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ መረባረብ ፣
- ዝርዝር ተግባራትን በደንብ ፈትሾ መለየት ፣ ዝርዝር ተግባራትን በሚለኩ አኳኋን መቅረጽ
- ለዝርዝር ተግባራቱ በቂ የገንዘብ፣የማቴሪያልና የሰው ኃይል መኖሩን ማረጋገጥ፣
- የዝርዝር ተግባራቱን የአፈጻጸም ጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት፣
- የዝርዝር ተግባራትን የክትትል ስልት መቀየስ፣

ክትትል የአንድ ኘሮግራም ወይም ድርጅት ዝርዝር ተግባራትን የአፈጻጸም ብቃት ለመለካትና በሂደት ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የሚስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ዕድል ከመስጠቱም ባሻገር በውጤት ፋይዳ ሥራዎች እንዲናተኩርና የመማማሪያ፣የግልፅነትና የተጠያቂነት ባህል እንዲዳብር ይረዳል፡፡

እንደሚታወቀው ኘሮግራሞች፣ኘሮጀክቶችና የሥራ እቅዶች መከታተልና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃዎች ለመውሰድ ወጥ የሆነ የክትትል መርሆ ወይም ስልት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የሚከተሉትን ዋና ዋና የክትትል መርሆዎችን ወይም ስልቶች ተፈጻሚ በማድረግ የክትትል ሥርዓቱን በጠንካራ ልማት ላይ ማነጽ ይቻላል፡፡

- የታቀደው ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እየተከናወነ መሆኑንና ለሥራው መሳካት የተመደበው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ግብዓቶች በትክክል በሥራው ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- የሥራ ዕቅዱን የሚያስተጓጉሉ ያልተጠበቁ መሠናክሎች ምን እንደሆኑ በደንብ በመለየት አፋጣጥ የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

- በፕሮግራም ወይም በፕሮጀክት ደረጃ የሚካሄድ የአፈጻጸም ክትትል የሚያተኩረው የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ ሂደቶችን በመለከት፣ የሥራ ውጤቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ማለቃቸውንና የውጤት አመልካቾችን በደንብ ማመላከት ያስፈልጋል፣
- ውጤታማ ክትትል ለማድረግ ሥራው ከመሠራቱ በፊት የነበረውን ሁኔታ የሚያሣይ መረጃ፣ብቃትና ውጤት አመልካቾች፣ መረጃን ለማሰባሰብ የሚያስችሉ አሠራሮችን ለምሣሌ በዕቅድ የተደገፈ የመስክ ጉብኝት፣የባለድርሻዎችን የምክክር መድረክ ፣የክትትል ሪፖርቶች እንዲሁም የግልጽነትና የተጠያቂነት መርሆ መሠረት የአጋሪነትና የአፈጻጸም ስልቶችን ማካተት አስፈላጊ ነው፡፡

በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተ የክትትል መርህ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡

- የሥራ ዕቅዱን የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም የተሻለ እንደሆን ያደርጋል፡፡
- በሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት የተስተወሉ ዋና ዋና ችግሮችን በዝርዝር በመለየት አማራጭ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡
- በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሣኔዎችን ለመወሰን ይጠቅማል፡፡
- የተጠያቂነት አሠራርን ለማስፈን በር ይከፍታል፡፡
- ክልላዊ፣ብሔራዊና ክፍለ አሁገራዊ የክትትል ዘዴዎችን ክህሎቶችን ለመጋራት የራሱን ድርሻ ያበረክታል፡፡
- መልካም አሠራሮችንና ተሞክሮችን ለማጠናከርና ለማሰፋፋት ይጠቅማል፡፡
- ችግር ፈቺና በጐ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡
- የክትትል ሥርዓትን ተራማጅ ከማድረግ አኳያ አቅምን ያጐለብታል፡፡

## 3.2 <u>የግምገማ መርሆና አስፈላጊነት</u>

ወጥ የሆነ የልማት እቅድ፣ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ከተመደበለት ግብዓቶች አጠቃቀም ማለትም ከሰው ኃይል፣ቁሳቁስና ገንዘብ አንፃር ያመጣው የስኬት ደረጃ፣ጠቀሜታ ፣ውጤታማነት ያስከተለው ወይም ልያስከትል የሚችለው የአጭርና የረዥም ጊዜ ፋይዳ ፣ቀጣይነት ወ.ዘ.ተ የሚቃኝበትና የተገኙ ተሞክሮዎች የሚዳሰስበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግምገማ የአንድን የልማት ኘሮግራም ወይም ኘሮጀክት አጠቃላይ አፈጻጸም

ለመከታተልና የግብ ስኬት ለማሳካት የሚያስችሉ የግንዛቤ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚረዳ ስልት ከመሆኑም ባሻገር የኘሮግራሙን ወይም የኘሮጀክቱን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ፣ ያመጣው ውጤቶችን ታኣማንነታቸውንና ዘላቂታማነታቸው ለማጤን የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በመሆኑም ግምገማ ኘሮግራሞች ወይም ኘሮጀክቶችን የሥራ ዕቅዶች ግልጽና ልለኩ የሚችሉ የውጤት ፋይዳዎችን ለማውጣት የተዘረጉ ስልቶችን፣የተገኙ ውጤቶች በተጠቃሚዎች ዘንድ ያመጣውን ወይም ልያመጣ የሚችለውን የአጭርና የረዥም ጊዜ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖችን በጥልቀት በመመርመር በቀጣይነት ልወሰዱ ሚገቡ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፡፡

በመሆኑም የኘሮጀክቶችን ወይም የኘሮግራሞችን የመካከለኛና የመጨረሻ ጊዜ ግምገማን የተሳካና ወጥ ለማድረግ ዋናውና ወሳኝ ጉዳይ ቅድሚያ ሁኔታዎችንና ስልትን መዘርጋት ነው፡፡ በመሆኑም ግምገማን ለማካሄድ በቅድሚያ ልሟሉና ልዘረጉ የሚገቡ ሂደቶችና ስልቶች በዋናነት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- የግምገማን ዓላማና አስፈላጊነት ግልጽና በማያሻማ መልኩ መቅረጽ፣
- ለግምገማ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማደራጀት፣
- የግምገማውን የጊዜ ሠሌዳ ፣ግምገማው የሚከናወንበት ቦታና ሎጀስቲካ ማመቻቸት፣
- የግምገማን ስልትና ሂደት የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት በማስገባት መንደፍ፣
    - ዓላማን
    - አስፈላጊነት
    - ልከናወኑ የታቀዱትን ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራትን ብዛት፣መለኪያቸውን፣ የአፈጻጸም ደረጃቸውን መስፈርቶች፣ የሚጠበቁ ውጤቶችን በደንብ መለየት፣
    - ለግምገማ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፣የቁሳቁስና የገንዘብ ፍላጎት ማዘጋጀት፣
    - የመጀመሪያ የሥራ ዕቅድን ተከታታይ ሪፖርቶችንና ሌሎችን ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎችንና ማሰባሰብና ማደራጀት፣
    - ተገቢውን የግምገማ ዘዴን ማለትም የመስክ ጉብኝት፣የቡድን ውይይትንና ቃለ-መጠይቆችን ማዘጋጀትን
    - ከሠነዶች፣ከሪፖርቶችና እንዲሁም በመስክ ደረጃ የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚደራጁበትና የሚተነተንበትን ስታቲስትካዊ ስልት በደንብ መለየት፣

## 3.3 የሪፖርት አቀራረብና ግብረ - መልስ መስጠት፣

ክትትልና ግምገማ ከተደረገ በኋላ በቀጣይነት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ አሳማኝ፣ወቅታዊና ግልጽ የሆነ ሪፖርትና ግብረ-መልስ ለሚመለከታቸው አካላት ማሠራጨት ነው፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ባለው ክፍል የሪፖርት አቀራረብና ግብረ-መልስ መስጠት ጠቀሜታዊና ሂደት ለማመላከት ጥረት ተደርጓል፡፡

- የአንድ የልማት ዕቅድ የአፈጻጸም ደረጃው በምን ሁኔታ እንደሚገኝ በየጊዜው የሚደረግ ዘገባ ሲሆን የታቀዱ ሥራዎች በአንድ በተወሰነ ጊዜ ክንውናቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ለዕቅድ ክንውን እንደወሳኝ ግብዓት ሆነው የሚያገለግል የሰው ኃይል፣የቁሳቁሶች የፋይናንስ አፈጻጸም ከዕቅድ አኳያ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ፣በአፈጻጸም ወቅት የታዩና የተከሰቱ ችግሮች ምን እንደሆኑ ፣የተወሰዱ እርምጃዎች፣ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣የተገኙ ውጤቶችና ሌሎችንም በሪፖርት መልክ ማዘጋጀት አለባቸው፣
- የልማት ዕቅድን ወይም ወጥ የሆነ ኘሮግራምንና ኘሮጀክትን የአፈጻጸም ደረጃውን በጥራትና በመጠን በመመርመር ተግባራዊ የሆነውን ከታቀደ ጋር ለማነፃፀር
- በኘሮጀክት አፈጻጸም ላይ የተገኙ ግኝቶች፣
- በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በደንብ በመለየት ግልጽ ማድረግ ፣
- በአፈጻጸም ሂደት ላጋጠሙ ችግሮች በቀጣይነት የመፍትሄ ሀሣብ ለማስቀመጥ፣

<u>የሪፖርት ዓይነት ከተጠቃሚዎች አኳያ የሚከተሉት ከግምት ውስጥ በማስገባት መዘጋጀት አለበት፣</u>

- ግልጽና በማያሻማ ቋንቋ ማዘጋጀት
- ሪፖርት ሲዘጋጅ ለማን መሠራጨትና ግብረ-መልስ መስጠት እንዳለበት ከግምት ማስገባት አለበት፣
- በግምገማና በክትትል ላይ የተመሠረተ ፣ግነት የሌለበትና ትክክለኛ መሆን ፣
- በታቀዱለት ጊዜ የሚዘጋጅና ወቅታዊና አሣማኝ መሆን
- ዮተገኙት ግኝቶችንና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን አካቶ ይዘቱ ሳይዛባ በዕቅድ መሠረት ማዘጋጀት፣